በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በትምህርት ሚኒስቴር የአስራ አንድ አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2009

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ............................................................ i

ማጠቃለያ (Executive Summary) ............................................................ I

ክፍል አንድ ............................................................ 1

መግቢያ ............................................................ 1

የትምህርት ሚኒስቴር አመሰራረት ............................................................ 1

የትምህርት ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ ............................................................ 3

የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተግባርና ሃላፊነት ............................................................ 5

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ............................................................ 6

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ............................................................ 7

ሰንጠረዥ1. የትምህርት ሚኒስቴር የሶስት አመት በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ፡፡ ............................................................ 7

ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የተመደበው በጀት እና የወጣው ወጪ ............................................................ 8

ሰንጠረዥ2. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ የሁለት አመት በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ፡፡ ............................................................ 8

የኦዲቱ ዓላማ ............................................................ 8

ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Audit Area) ............................................................ 8

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ............................................................ 9

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ............................................................ 9

የ11 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ የአሰራር ሥርዓት ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ /Process Description/ ............................................................ 10

ምስል 1. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የአሰራር ሥርዓት ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ፡፡ ............................................................ 10

ክፍል ሁለት ............................................................ 11

ግኝቶች ............................................................ 11

2.1. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ዕቅድ ዝግጅት ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የተስማሙበት ግልጽና ሥራዎች የሚከናወኑበት የጊዜ ገደብ የተቀመጠላቸው አሳታፊና ሊተገበር የሚችል ስለመሆኑ፤ ........ 11

የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ የፈፃሚ አካላትን ድርሻ የሚለይ፣ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ እና በየጊዜው የሚገመገም መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 11

የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 13

የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ መሆኑ በተመለከተ፣ ........ 14

በባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፤ ........ 19

2.2. የአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በእቅዱ መሠረት በመተግበር የተማሪ ቅበላ ሂደቱ በተቀመጠለት የዕቅድ መርሃ ግብር መሰረት መከናወኑን፤ ........ 20

ሊያጋጥሙ የሚችሉ የግንባታ ሥጋቶችን (Risks) ማጥናትና ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግን በተመለከተ ........ 20

የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በሰው ሃይልና በቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች መደራጀታቸውን በተመለከተ፣ ........ 22

ግንባታውን አስመልክቶ የአካባቢና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት የተከናወነ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 23

በግንባታው ምክንያት ለሚነሱ ተነሽዎች የተያዘው በጀት በበቂ ጥናት ላይ አለመመስረቱ፣ የሚከፈል የካሳ ክፍያ እና የካሳ ክፍያ መዘግየቱን በተመለከተ፤ ........ 24

**ምስል 2. ለካሳ ክፍያ የተያዘው በጀት ከተከፈለው ጋር ማነጻጸሪያ።** ........ 27

**ሰንጠረዥ3. ለካሳ ክፍያ የተያዘው በጀት ከተከፈለው ጋር ማነጻጸሪያ፡፡** ........ 27

የውሃ እና የኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት አቅርቦትን በተመለከተ፣ ........ 31

**ሰንጠረዥ4. ለካሳ ክፍያ የተያዘው በጀት ከተከፈለው ጋር ማነጻጸሪያ፡፡** ........ 31

የስታንዳርድ እና ዝርዝር ዲዛይን (Standard and Detail Design) ስራዎች በተመለከተ፣ ........ 33

2.3 የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ግብዓቶች እና ሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት በዕቅድ መርሃ ግብር መሰረት መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 36

የአስራ አንድ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ተጠናቆ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማስጀመር መሟላት የሚገባቸው ግብዓቶችን በተመለከተ፣ ........ 36

ክፍል ሦስት ........ 38

የመደምደሚያ ሃሳቦች ........ 38

ክፍል አራት ........ 40

የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 40

አባሪ 1 ........ i

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ........ i

የትምህርት ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር አባሪ 2 ........ 1

# ማጠቃለያ (Executive Summary)

መንግስት በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን አስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎችን በማስገንባት በ2010 የትምህርተ ዘመን እያንዳንዳቸው 1500 አስራ አንዱ በድምሩ 16500 ተማሪዎች በመቀበል የመማር ማስተሩን ሂደት ለማስጀመር የታቀደው የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን በማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት መረጃዎችን በመከለስ፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና የግንባታ ሂደቱን በአካል ባሉበት በማየት ከዚህ በታች የታዩትን ዋና ዋና ግኝቶች እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦችን ታይተዋል፡፡

- የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ዕቅዱን ለመተግበር የሚያስችል የዕቅድ ትግበራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት እንዲሁም በዓመት ተከፋፍሎ ሊተገበር በሚችል መልክ ሊቀመጥ ይገባል፡፡
- በኦዲት ወቅት አስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ለማከናወን የትግበራ መርሃ ግብር ያልወጣለት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት (ግንባታዎቹ በምዕራፍ ተከፋፍለው መቼ እንደሚሰሩ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ፣ ፕሮጀክት ፅ/ቤቶች የት እንደሚቋቋሙ፣ ለካሳ ክፍያ የተያዘው ወጪ፣ ለቅድመ ግንባታ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችና ወጪዎች፣ ባለድርሻ አካላት ሚናቸው መለየቱን…) የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ተዘጋጅቶ በመሪ ዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎችን የግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ቢዘጋጅም የግንባታ ግብዓት ሆነ የላብራቶሪና የመጽሐፍት ግዥ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ምክንያት ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ካሣ ሊከፈል ይገባል፡፡ ካሳ የተከፈላቸው ተነሽዎች የካሣ ክፍያ ከተፈፀመላቸው በኋላ ከቦታቸው በተቀመጠው ቀነ ገደብ መነሳት አለባቸው፡፡

- ይሁን እንጂ ለአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ምክንያት ከግንባታው ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ክፍያ ያልተከናወነ እና ካሳ የተከፈላቸውም የአካባቢ ነዋሪዎች በተቀመጠው ቀነ ገደብ ከቦታው ያልተነሱ መሆኑን በኦዲት ወቅት

ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም፡-

♦ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎችን የግንባታ ኘሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ቀሪ ሂደቱ ዋነኛው መሪ ዕቅዱ (Master Plan) መሰረት በማድረግ እና የድርጊት መርሃ ግብር በማውጣት ተግባራዊ ሊደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የዘገዩ ስራዎች የሚካካሱበትን መንገድ በመቀየስ በዕቅዱ መሰረት የተማሪዎች ቅበላ የሚከናወንበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡

♦ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ የፕሮጀክት እቅድ ትግበራው ሂደቱ ገና በጅምር ላይ ስለሆነ ለአንደኛውም ሆነ ለቀሩት የግንባታ ምዕራፎች በትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደቱ በዘላቂነት እንዳይቀጥል ሊከሰቱ የሚችሉ ሥጋቶች ተለይተው እንዲቀመጡ እና እንዳይከሰቱ ቅድመ ጥንቃቄ ስራዎችም ሊሰሩ ይገባል፡፡

♦ ለአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ምክንያት ከግንባታ ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ክፍያ ያልተከናወነላቸው ነዋሪዎች በህጉና በመመሪያው መሰረት እንዲከፈል እና ለካሳ ክፍያ ተብሎ በጥቅል የተላኩ ሂሳቦች እንዲሁም እስከ ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም ያልተወራረዱ ሂሳቦች በአስቸኳይ ሊወራረዱ እና በካሳ ምክንያት ያላግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ተጣርቶ በአስቸኳይ የሚመለስበት ሁኔታ ሊመቻች እንዲሁም ወደፊትም የሚከፈሉ የካሳ ክፍያዎች በካሳ አዋጁ፣ ደንብ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት ሊፈጸሡም እና ከህግ ውጭ እንዲከፈል የተደረገው ሂሳብ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ትምህርት የሰው ልጅን በእውቀት፣ በግንዛቤ፣ በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት፣ በሥነ-ውበትና በእሴት እንዲሁም በችሎታና በክህሎት በማነጽ ለራሳቸውና ለኅብረተሰብ ሁለንተናዊ እድገት ፍሬያማ ተሳትፎ ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ ትምህርት በሰው ህይወት እና አስተሳሰብ ላይ ሂደታዊ (Progressive Processes) የሆነ ለውጥ ፈጣሪ መሳሪያ ሲሆን በግለሰብና በኅብረተሰብ ተስተጋብሮት ለአጠቃላይ ኅብረተሰብ ህልውናና እድገት ቁልፍ ሚና አለው፡፡ ስለዚህ ለአንድ ሀገር እድገት እና ብልጽግና አንቀሳቃሽ ሞተር የሰለጠነ የሰው ኃይል የማፍራት ስራ በመሆኑ የትምህርት ዘርፉን ለማሳደግ ትምህርት ቤቶችንና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መገንባት፣ ማስፋፋትና ማብቃት ወሳኝ ስራ ነው፡፡ ስለሆነም መንግስት ለትምህርት ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በከፍተኛ በጀት የከፍተኛ ትምህርትን ጨምሮ በየደረጃው የሚያገለግሉ ተቋማትን አስገንብቷል፣ እያስገነባም ይገኛል፡፡

2. በዚህም መሰረት መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊ ስርጭት መስፋፋት በሰጠው የተለየ ትኩረት በአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አስር ተጨማሪ ተቋማትን በመገንባትና የነባር ተቋማትን የማስፋፋት ስራዎች በመስራት ዘርፉ የበለጠ እንዲስፋፋ በማድረግ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰለጠኑ ዜጎች ቁጥር ከፍ ለማድረግ ሲሰራ ነበር፡፡

3. በሁለተኛው የዕድገትና ትርንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም መንግስት በሀገሪቱ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት እንዳይኖር ለማስቻል በከፍተኛ በጀት አዲስ አስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎችን በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች እያስገነባ እንዲሁም ነባር ዩኒቨርሲቲዎች በማስፋፋትና በማጎልበት ላይ ይገኛል፡፡

## የትምህርት ሚኒስቴር አመሰራረት

4. ዘመናዊ ትምህርት ማዕከላዊ መንግስታትን ለማጠናከርና አዲስ ስልጣኔን ከውጭ ለማስገባት የሚጠቅም መሆኑ ስለታመነበት ከስድስት ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው ወንዶችና ሴቶች ትምህርት ቤት የመግባት ግዴታ እንዳለባቸው ወላጆች ልጆቻቸው እንዲማሩ ማበረታታት እንደሚገባቸው የሚያመለክት የመጀመሪያው የትምህርት አዋጅ በ1898 ዓ.ም ወጣ፡፡ አፄ ምኒልክን የተኩት ንግስት ዘውዲቱ የትምህርት

ዓላማ ክፉና በጎ የሚለይበት ንጉስንና ፈጣሪ የሚፈራበትን ዕውቀት ያስገኛል በሚል በ1921 ዓ.ም ሁለተኛው የትምህርት አዋጅ እንዲወጣ አድርገዋል፡፡

5. አፄ ሀይለ ስላሴ የአገሪቱ ንጉስ ሲሆኑ ዘመናዊ መንግስት ለመመስረት በነበራቸው ዓላማ በዚያው በነገሱበት ዓመት በ1923 ዓ.ም ቀደም ሲል የትምህርቱን ሥራ እንዲመራ ያቋቋሙት የትምህርት ዋና ዳይሬክቶሬት (Directorate General of Public Education) ወደ ሚንስቴር መስሪያ ቤት በማሳደግ የትምህርትና ስነ ጥበብ ሚንስቴርን አቋቋሙ፡፡

6. የትምህርቱ ሥራ እየሰፋ ሲሄድ አወቃቀሩንና የፋይናንስ አቋሙን ለማጠናከር ሲባል በ1935 የትምህርት ሚኒስቴርን ሥልጣንና ተግባር የሚወስን አዋጅ እንዲሁም በዚሁ ዓመት የትምህርትና ስነ ጥበብን ጉዳይ የሚከታተልና የሚመራ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ወጣ፡፡

7. በ1966 አብዮት መከሰት ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ በትምህርቱ ዘርፍ የነበሩት ችግር በመሆኑ በ1967 ደርግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ የትምህርቱን ስርዓት ለመለወጥ አዲስ አደረጃጀት ተጠንቶ ስራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡ ሥነ ጥበብ ወደ ስፖርትና ባህል ሚኒሰቴር ሲሄድ የከፍተኛ ትምህርት ሥራ ዘርፎች ራሳቸውን ችለው በኮሚሽን ደረጃ እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም ትምህርት ሚኒስቴር በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በአስር መምሪያዎች በረዳት ሚንስትሮችና በሚኒስቴር ዴኤታና በሚኒስትር ይመራ የነበረው የትምህርት ሥራ ወደ አራት መምሪያዎችና ወደ አምስት ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡

8. በ1983 ኢ.ህአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ተንሰራፍተው የቆዩ ችግሮችን ለመፍታት የትምህርት ፖሊሲው መቀየር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት በአዋጅ 41/85 የከፍተኛ ትምህርትን ጨምሮ አስራ ሰባት ተግባራት እንዲኖሩት በማድረግ ተቋቁሟል፡፡ በአዋጅ 4/87 እና 256/94 እነዚህ ተግባራት ወደ አስራ አምስት ተግባራት ተቀንሰው ትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለአቅም ግንባታ ሚኒስቴር እንዲሆን ተደረገ፡፡

9. በኋላም የሀገራችን ትምህርት ለሀገር ሁለንተናዊ ልማት የሚበጁ ዜጎችን እንዲያፈራ ለማስቻል የተለያዩ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲዎች ሲቀረፁ ቆይተው በኢትዮጵያ ህዝቦች የእድገት ፍላጎትና ዓለም አቀፋዊ ትስስር መሰረት ተቋማት አስተማማኝ የማስፈፀም አቅም እንዲኖራቸው ለማስቻል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ተግባር እንደገና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መስከረም 25, 2008 ዓ.ም በአዋጅ 691/2003 እንደገና በአዋጅ 916/2008 ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

## የትምህርት ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ

### ራዕይ

10. ብቁ ዜጋ የሚያፈራ፣ ጥራትና ፍትኃዊነትን ያረጋገጠ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት እስከ 2012 ሙሉ በሙሉ ገንብቶ መገኘት፡፡

### ተልዕኮ

11. የትምህርት ዘርፉን የማስፈጸም አቅም በመገንባት፣ የብቃት መለኪያዎችን በማውጣትና በማስጠበቅ፣ ደረጃውን የጠበቀ የከፍተኛ ትምህርት በማስፋፋትና ተግባራችንን በአህዝቦት ሥራ በማገዝ ጥራት ያለው ውጤታማ፣ ፍትሀዊና አሳታፊ የትምህርት ስልጠና ሥርዓት ማረጋገጥ ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር በአዋጅ ቁጥር 916/2008 መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፣

- የትምህርትና ሥልጠና ስታንዳርድ ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፣ ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ አጠቃላይ የሥርዓተ ትምህርት ማእቀፍ ያዘጋጃል፣ የመምህራንን አነስተኛውን የትምህርት ብቃት መለኪያ ያወጣል፣ እንዲሁም የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሊያሟሉ የሚገባቸውን አነስተኛውን ደረጃ ያወጣል፡፡
- የከፍተኛ ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል፡፡
- በየደረጃው ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መሰጠቱን ያረጋግጣል፡፡

- የሀገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ያደረጉ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል፣ የውጤት ሪኮርዶች ይይዛል፣ የውጤት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
- የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂን ይቀርጻል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡
- የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ አፈጻጸም ፍትሃዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
- ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፡፡
- የፌዴራል መንግሥቱ ሕጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፡፡
- የጥናትና ምርምር ተግባሮችን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ያሰራጫል፡፡
- የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
- ለክልሎች እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፣ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተቀናጀ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
- ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈጻሚ አካላት አፈጻጸም በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡ አደረጃጀቶቻቸውን እንዲሁም የሥራ ፕሮግራሞቻቸውንና በጀቶቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲቀርቡ ይወስናል፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ የፌዴራል ወይም የክልል አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣ ስለሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡
- በአዋጁ መሰረት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የሆነው የትምህርት ሚኒስትር የሚመራውን ሚኒስቴር የመወከል፣ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ የማዋል፣ የተፈቀደለትን በጀት በሥራ መርሃ ግብሩ መሠረት ገንዘብ ወጪ የማድረግ በሚኒስቴሩ መስሪያ ቤቱ ውስጥ የአፈጻጸም አመራር ሥርዓት ተግባራዊ የማድረግ

ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተግባርና ሃላፊነት

13. የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ለከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሆኖ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናል፡፡

- ግንባታው የሚፈፀምበትን ዝርዝር የፕሮጀክት ሰነድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፡፡
- የፕሮጀክት ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፡፡ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፡፡
- የአማካሪዎችንና የተቋራጮችን ምርጫ ያስፈፅማል፡፡
- በአማካሪዎች የተዘጋጁ ዲዛይኖች (ስታንዳርድና ዝርዝር ዲዛይኖች) በውይይት ዳብረው እንዲፀድቁ ያደርጋል፡፡
- የግንባታ ሥራ ተቋራጮችን ምርጫ ከከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር ይፈፅማል፡፡
- ለሥራ ተቋራጮች በዲዛይኑና በግንባታው አፈፃፀም ላይ ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ ያደርጋል፡፡
- ለሥራ ተቋራጮች፣ ለአማካሪዎችና ዕቃ አቅራቢዎች በውለታውና በሕግ አግባብ መሠረት ክፍያ ይፈፅማል፡፡
- ይዞታቸው ለዩንቨርስቲዎች ግንባታ በመሰጠቱ ለሚነሱ ነዋሪዎች በክልሉ የካሳ ክፍያ ታሪፍ መሰረት ክፍያ እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡
- ለዩንቨርስቲዎች የሚያገለግል የውሃ፣ የኤሌክትሪክ ሃይልና የቴሌኮም አገልግሎት እንዲሟላ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በጋራ ይሰራል፡፡
- ለግንባታ የሚያስፈልጉ የአርማታ ብረትና ሲሚንቶ ያቀርባል፣ ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ ግንባታ ሳይት መጓጓዛቸውንና ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡
- የትምህርት መሣሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶች ዝርዝር ስፔሲፊኬሽንና ስታንዳርድ እንዲዘጋጅ ግዥው እንዲፈፀም ያደርጋል፣ በበቂ መጠንና ጥራት በየዩኒቨርስቲው መሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡
- የሚገነቡ ሕንፃዎችን ዓይነት፣ ብዛትና፣ የግንባታ ቅደም ተከተል አዘጋጅቶ እንዲገነቡ ያደርጋል፡፡
- የመሰረተ ልማትና የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ፕላንት ግንባታ ቢቻል ከግንባታው በፊት አለዚያም ጎን ለጎን እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

- የአማካሪዎች ፎረም በማቋቋም በግንባታው አፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
- ዩንቨርስቲዎች ፕሮጀክቱን ለመረከብ በሚችሉበት ቁመና ላይ ሲደርሱ ዝርዝር የርክብክብ ሰነድ አዘጋጅቶ ፕሮጀክቱን ያስረክባል፡፡
- ለአዳዲሶቹ ዩንቨርስቲዎች የተፈቀደውን የግንባታና የትምህርት መሳሪዎች ግዥ በጀት የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ ሥራ ላይ ያውላል፣ ወቅቱን ጠብቆ ሂሳቡ መዘጋቱን ያረጋግጣል፡፡ ሪፖርትም ያቀርባል፡፡
- ለፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ተገቢው የሰው ሃይል እንዲሟላ ያደርጋል፡፡
- ግንባታውንና የግብዓት አቅርቦቱ በአግባቡ መፈጸሙን ለመከታተል የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፡፡
- እንደውለታቸው በማይፈፅሙ ሥራ ተቋራጮችና አቅራቢዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

14. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው የተቋሙ የበላይ አመራር በሆኑ በአንድ ሚኒስትር እና አራት ሚኒስትር ዴኤታዎች ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ የትምህርት ሚኒስቴር በሚኒስቴር ዴኤታዎች የሚመሩ አራት (የአጠቃላይ ትምህርት፣ የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እና የስራ አመራርና አስተዳደር) ዘርፎች አሉት፡፡ የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ በስሩ 11 ዳይሬክቶሬቶች ሲኖሩት የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ እና የትምህርት ኢንፎርሜሽንና ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማዕከል ለዚህ ዘርፍ ተጠሪ ናቸው፡፡

15. የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ በስሩ ሦስት ዳይሬክቶሬቶች አሉት፡፡ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ፣ የትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል፣ የኤዱኬሽናል ሪሰርች ኔትዎርክ ዳታ ሴንተር እና ዩንቨርሲቲዎች ለዚህ ዘርፍ ተጠሪ ናቸው፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ሥር ሁለት ተቋማት (የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፣ እና የፌዴራል ቴክኒክና

ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም) ተጠሪ ናቸው፡፡ የሚኒስቴሩ ድርጅታዊ መዋቅር **በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡**

16. በኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ማእረግ የሚኒስትር ቢሮ ሃላፊ የሚመራው የስራ አመራርና አስተዳደር ዘርፍ በስሩ አስራ አንድ ዳይሬከቶሬቶች እና የውጭ ግንኙነትና ስኮላር ሺፕ ጽ/ቤት አሉት፡፡ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት፣ የሥነ-ምግባር መከታተያና የቅሬታ ማስተናገጃ ጽ/ቤት እና የሥርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት በቀጥታ ለሚኒስትሩ ተጠሪ ሆነው አገልገሎት ይሰጣሉ፡፡

## የሰው ሃይል

17. የትምህርት ሚኒስቴር 806 ቋሚ ሠራተኞች በመዋቅር የጸደቀለት ሲሆን እስከ ህዳር ወር 2009 ዓ.ም ድረስ 639 (79.28%) ቋሚ ሠራተኞች ነበሩት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ፕሮፌሽናል የሆኑ ወንድ 235 ሴት 56 ድምር 291 እንዲሁም ፕሮፌሽናል ያልሆኑ ወንድ 145 ሴት 203 በድምሩ 348 በጠቅላላ ወንድ 380 እና ሴት 259 በድምር 639 ሰራተኞች አሉት፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

18. የትምህት ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት የካፒታል እና መደበኛ በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ 1 እና ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት በሰንጠረዥ 2 ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | የተፈቀደው በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2006 | 1,062,996,169.33 | 464,935,106.15 | (43.74%) |
| 2007 | 638,233,603.00 | 410,520,090.46 | (64.32%) |
| 2008 | 1,194,402,650.28 | 907,368,750.16 | (75.97%) |

<u>ሰንጠረዥ1.</u> **የትምህርት ሚኒስቴር የሶስት አመት በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ፡፡**

ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የተመደበው በጀት እና የወጣው ወጪ

| በጀት ዓመት | የተፈቀደው በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2008 | 1,762,000,000 | 439,404,400.89 | (24.94%) |
| 2009 | 2,216,753,170 | 216,731,461.12 (እስከ ህዳር 30 2009) | (9.78%) |

ሰንጠረዥ2. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ የሁለት አመት በጀት እና ስራ ላይ የዋለው ማነጻጸሪያ፡፡

19. ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው የአስራ አንድ ግንባታ ፕሮጀክት የፋይናንስ አፈጻጸም ሲተነተን የ2008 በጀት አመት አፈጻጸም 24.94% ሲሆን 2009 በጀት አመት እስከ ህዳር 30 2099 ዓ.ም ድረስ ከተመደበው በጀት 9.78% ሥራ ላይ ውሏል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

20. የኦዲቱ ዓላማ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን በመንግስት ተገንብተው በ2010 የተማሪ ቅበላ እንዲጀምሩ ታስበው የሚገነቡ አዲስ አስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ከባለፉት የተገነቡት የአስራ ሶስቱ እና የአስሩ ዩኒቨርስቲ ፕሮጀክት ግንባታዎች አፈጻጸም ላይ የታዩት በርካታ ችግሮች በአስራ አንዱ ዩንቨርስቲዎች ፕሮጀክት ግንባታ በድጋሚ እንዳይከሰቱ ለማስቻል ሲሆን በዚህ ዙሪያ የሚከሰቱትን የአሠራር ክፍተቶችን ለይቶ በማውጣት ክፍተቶቹ የሚቀረፉበት የማሻሻያ ሀሳቦችን (Recommendations) ለማቅረብ ነው፡፡

## ለኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Audit Area)

21. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

*"የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም፣ የግንባታ እና ሌሎች ግብዓቶች ለማሟላት የታቀደው ዕቅድ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ መሆኑን መገምገም"*

የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

22. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም:-

1. የ11 ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ዕቅድ ዝግጅት ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የተስማሙበት ግልጽና ሥራዎች የሚከናወኑበት የጊዜ ገደብ የተቀመጠላቸው፣ አሳታፊና ሊተገበር የሚችል መሆኑን መገምገም፣
2. የ11 ዩንቨርስቲዎች ግንባታ በዕቅዱ መሠረት በመተግበር የተማሪ ቅበላ ሂደቱ በተቀመጠለት የዕቅድ መርሃ ግብር መሰረት እየተከናወነ መሆኑን መገምገም፣
3. የ11 ዩንቨርስቲዎች የግንባታ ግብዓቶች እና የሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት በዕቅዱ መርሃ ግብር መሰረት የሚከናወን መሆኑን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

23. ለተመረጡት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 25 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቋቋመበት አዋጅ፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስትራቴጅክ ዕቅድ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር የተቋቋመው የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባር፣ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ እቅድ፣ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ የድርጊት መርሃ ግብር፣ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ስታንዳርድ እና ዝርዝር ድዛይን፣ የፕሮጀክቱ የግንባታ ውሎች እና ከዚህ በፊት የተገነቡት የአስር እና አስራ ሶስቱ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ እቅድ እንዲሁም አፈጻጸም መልካም የሥራ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡


## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

24. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008

በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ የኦዲት ሽፋኑ ከ2006 እስከ 2008 ያለውን የሦስት በጀት ዓመት አፈጻጸም ነው፡፡ ለክዋኔ ኦዲቱ በተመረጡት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት መረጃዎቹ ተተንትነዋል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡

25. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቋቋመው ፕሮጀክት ግንባታ ጽ/ቤት ሲሆን ፕሮጀክት ፅ/ቤቶች በሚገኙባቸው ክልሎች መካከል በናሙና ተመርጠው በታዩት በሦስት ክልሎች (አማራ፣ ደቡብና ትግራይ) የሚገኙትን ሦስት ዩኒቨርሲቲዎች (እንጅባራ፣ ወራቤ እና ራያ) የፕሮጀክት ግንባታ ጽ/ቤቶችን በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በግንባታ ፕሮጀክቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎችን ጠይቆ በመከለስ እና በየሳይቶቹ እየተገነቡ ያሉትን ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ሂደት አፈጻጸማቸውን በናሙና መርጦ በአካል በመመልከት ነው፡፡

## የ11 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ የአሰራር ሥርዓት ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ /Process Description/




ምስል 1. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የአሰራር ሥርዓት ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### 2.1. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ዕቅድ ዝግጅት ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የተስማሙበት ግልጽና ሥራዎች የሚከናወኑበት የጊዜ ገደብ የተቀመጠላቸው አሳታፊና ሊተገበር የሚችል ስለመሆኑ፤

**የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ የፈፃሚ አካላትን ድርሻ የሚለይ፣ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ እና በየጊዜው የሚገመገም መሆኑን በተመለከተ፤**

26. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ የፈፃሚ አካላትን ድርሻ የሚለይ እና የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባል፡፡ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ በሁሉም አካላት ሊገመገምና አስተያየት ሊሰጥበት ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ እቅድ ዝግጅት፡-

- ዩኒቨርሲቲዎቹ ሊገነቡ በታቀደባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን (የከተማ፣ የዞንና የወረዳ መስተዳደር አካላት፣ የክልሎች ውሃ ሃብት ቢሮዎች፣ የከተማ የውሃ አገልግሎቶች፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ወ.ዘ.ተ…) እና የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ/ አገልግሎት ያላሳተፈና አስተያየት እንዲሰጡበት ያልተደረገ መሆኑ፣
- ዕቅዱን ተግባራዊ የሚያደርጉ የፈፃሚ አካላትን ድርሻ በግልፅ ያልለየና አጋሮችና ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ሚና በግልጽ ለይቶ ያላስቀመጠ መሆኑ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር የሚገኘው ዋናው ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከአራት አጋሮችና ባለድርሻ አካላት ማለትም ከአማካሪዎች፣ ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፣ ከክልል ስራና ከተማ ልማት ቢሮዎች፣ ከክልል ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤቶች እንዲሁም ከየከተማው ከንቲባ ጽ/ቤቶች ጋር በመሆን በ2ኛው ሩብ ዓመት የጋራ ዕቅድ ለማከናወን ቢታቀድም ያልተከናወነ መሆኑ፣

- ግንባታው ከመጀመሩ በፊት መሰራት የሚገባቸው ቅድመ ዝግጅት ስራዎች በእቅዱ መሰረት በአስራ አንዱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ሳይቶች አለመሰራታቸው፣
- ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ሰነድ በሁለተኛ ሩብ ዓመት (ከጥቅምት እስከ ታህሳስ) ለመፈራረም ቢታቀድም ስምምነቱ የተፈረመው ዘግይቶ በሦስተኛው ሩብ ዓመት በየካቲት 11 2008 ዓ.ም መሆኑ፣
- የግንባታ ስራዎች በተባለው ጊዜ አለመጀመር፣ ለግንባታ ሳይቶች የሚያገለግሉ መንገዶች በወቅቱ አለመሰራት፣ የኤሌክትሪክ እና የውሃ አገልግሎት አለማግኘት

በወራቤ፣ እንጅባራ እና ራያ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ቦታዎች ላይ በመገኘት በተደረገው የመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. ግንባታን የሚመለከት ውል ከአማካሪዎችና ከተቋራጮች ጋር ተፈርሟል፡፡ ነገር ግን መዘጋጀት የነበረበት የጋራ ዕቅድ እንዳልተዘጋጀ እንዲሁም ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር በተለይም ከተቋራጮች፣ ከአማካሪዎች፣ ከአቅራቢዎችና ከከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በየሩብ፣ በግማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ የዕቅድ ክንውን ግምገማ ለማድረግ ቢታቀድም ያልተከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡

29. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከሚመለከታቸው ክልል ባለስልጣናት ጋር ተገቢው የግንዛቤ ልውውጥ የተደረገ እንዲሁም ከአቅራቢዎች እና ከተቋራጮች ጋር በሁለተኛው ሩብ ዓመት ከውይይትም አልፎ ስልጠና በመስጠት ስራው የተጀመረ ሲሆን ለወደፊቱ በኦዲት ሪፖርቱ አስተያየት መሰረት አጠናክረው እንደሚጠቀሙበት ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ እና በመዉጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ግኝቱን እንደግብዓትነት እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡

30. ኃላፊዎቹ ይህን ከላይ የተገለጸውን ምላሽ ቢሰጡም ከከተማ፣ ከዞንና ከወረዳ መስተዳደር አካላት፣ ከመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር አገልግሎት፣ ከክልሎች ውሃ ሃብት ቢሮዎች፣ ከከተማ የውሃ አገልግሎቶች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር የተደረገ የግንዛቤ ልውውጥ እና የጋራ የግንባታ ትግበራ ዕቅድ ስለመዘጋጀቱ ምላሽ አልሰጡም፡፡

31. በአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ እቅድ ዝግጅት ወቅት የእያንዳንዱን ባለድርሻ እና አጋር አካላትን ባለማሳተፉ እና ሚናና ሃላፊነታቸውን በዝርዝር ለይቶ ባለማስቀመጡ ሁሉም አካላት የሚጠበቅባቸውን ህገራዊ ግዴታቸውን እና

ኃላፊነታቸውን እንዳይወጡ ከማድረጉም በላይ በአካባቢው ማህበረሰቦችና ሃላፊዎች ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንዳይኖር፣ በቅንጅት የሚሰሩት ስራዎች በተፈለገው ፍጥነት እንዳይከናወኑ፣ እንዲጓተቱ እና ግንባታው በእቅዱ መሰረት እንዳይካሄድ ከማድረጉም በተጨማሪ መንግስትን ለአላስፈላጊ ወጪ እንዲዳረግ አድርጓል፡፡

**የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

32. የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት (ግንባታዎቹ በምዕራፍ ተከፋፍለው መቼ እንደሚሰሩ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ፣ ፕሮጀክት ፅ/ቤቶች የት እንደሚቋቋሙ፣ ለካሳ ክፍያ የተያዘው ወጪ፣ ለቅድመ ግንባታ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችና ወጪዎች፣ ባለድርሻ አካላት ሚናቸው መለየቱን…) የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ተዘጋጅቶ በመሪ ዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

33. በኦዲቱ ወቅት የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎችን የግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) የተዘጋጀ መሆኑ ቢረጋገጥም፡-

    ሀ. ማስፈፀሚያ እቅዱ ላይ የግንባታው ስታንዳርድ እና ዝርዝር ዲዛይን (Standard & Detail Design) በ2008 ዓ.ም በአንደኛው ሩብ ዓመት (ከሀምሌ 2007- መስከረም 2008 ዓ.ም) እንደሚጠናቀቅ ቢገለፅም ስታንዳርድ ዲዛይኑ ያለቀው በሰኔ 2008 ዓ.ም መሆኑ እንዲሁም ዝርዝር ዲዛይን ስራ (የዲዛይን ማጣጣም ስራ) እስከ ሕዳር 30/2009 ዓ.ም ድረስ አለመጠናቀቁን፣

    ለ. የአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በ2008 ዓ.ም በሁለተኛው ሩብ ዓመት (ጥቅምት-ታህሳስ 2008 ዓ.ም) እንደሚጀመር ቢታቀድም ዘግይቶ በሰኔ/2008 ዓ.ም መጨረሻ መጀመራቸውን፣

    ሐ. የትምህርት መሳሪያዎች ግዥ በ2008 በጀት ዓመት ሌተር ኦፍ ክሬዲት (Letter of Credit) በመክፈት ማለትም ስታንዳርድና እስፔሲፊኬሽን ማዘጋጀት፣ የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀትና ጨረታውን አየር ላይ በማዋል፣ አሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶችን የመለየት ስራ ማከናወን እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል የመፈራረም ስራዎች እንደሚጠናቀቁ ቢገለጽም እስከ መጋቢት 30/2008 ዓ.ም ድረስ ለትምህርት መሣሪያዎች ግዢ ለመፈፀም

የሚያስችል የመነሻ ስፔሲፊኬሽንና ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ በዩኒቨርስቲ ባለሙያዎች እየዳበረ እንደሆነ መገለፁ፣

መ. የማስፈጸሚያ ዕቅዱ ግንባታዎቹ እንደ አስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል በምዕራፍ ተከፋፍለው የትኞቹ ሥራዎች መቼ እንደሚገነቡ እና እንደሚጠናቀቁ ያልተገለጸ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱት ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ለተነሽዎች ካሳ ከተመደበው በጀት በላይ መከፈሉ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስህተት ሳይሆን ካሳ ገማች ኮሚቴው ወስኖ ያመጣው የግምት መጠን ከተያዘው በጀት በላይ በመሆኑና ይህንንም ለሚመለከተው አካል እንዳሳወቁ እንዲሁም በማስፈፀሚያ ዕቅዱ ላይ ግንባታዎች ቅደም ተከተል አልወጣላቸውም የተባለው በኦዲት ሪፖርቱ ማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ለወደፊቱም የእርምት እርምጃ እንደሚወሰድ ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ እና በመዉጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ግኝቱን እንደግብዓትነት እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል፡፡

35. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ላይ በተገለጸው መሰረት ተግባራዊ ባለመሆኑ እና ዕቅዱ ቅድሚያ መሰራት ያለባቸውን ስራዎች እና የባለድርሻ አካላትን ሚና በግልጽ ባለማስቀመጡ ሥራዎች እንዲጓተቱ ከማድረጉም በላይ ከተያዘው በጀት በላይ ወጪ እንዲወጣ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መሰረት አስራ አንዱም ዩኒቨርሲቲዎች የመጀመሪያ የግንባታ ምዕራፍ ተጠናቆ የመማር ማስተማር ሂደቱን ማስጀመርን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ መሆኑ በተመለከተ፣**

36. የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ዕቅዱን ለመተግበር የሚያስችል የዕቅድ ትግበራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት እንዲሁም በዓመት ተከፋፍሎ ሊተገበር በሚችል መልክ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

37. ይሁን እንጂ የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት፡-

- የካሳ ክፍያ እንዲፈጸም ለማድረግ በ2008 በጀት ዓመት አንደኛ ሩብ ዓመት በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ለማጠናቀቅ ቢታቀድም እስከ ህዳር 2009 ዓ.ም ድረስ የካሳ ክፍያው ለአስራ አንዱ (ለሁሉ) የግንባታ ሳይቶች በተባለው ጊዜ ተከፍሎ አለመጠናቀቁ፣
- በየሳይቱ የሚገኙ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በ2008 በጀት ዓመት በሁለተኛው ሩብ ዓመት የሰው ኃይል እንደሚሟላላቸው ቢታቀድም እስከ ህዳር 2009 ዓ.ም ድረስ ያልተሟላላቸው መሆኑ፣
- የተቋራጮች መረጣ እና ውለታ 55% በሁለተኛው ሩብ ዓመት 100% በ2008 በጀት ዓመት በሦስተኛው ሩብ ዓመት ለማከናወን በነሐሴ 2007 ዓ.ም እና በጥቅምት 2008 ዓ.ም ተከልሶ በተዘጋጀው እቅድ ቢታቀድም ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የዩኒቨርሲቲዎቹ የግንባታ ዲዛይን በ2008 በጀት ዓመት በአንደኛው ሩብ ዓመት እንደሚጠናቀቅ ቢገለጽም ዘግይቶ በሰኔ 28/2008 የተጠናቀቀ ሲሆን
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች (ሰላሌ፣ ጂንካ፣ ቀብሪ ደሃር፣ ኦዳ ቡልቱም፣ ራያ፣ ቦንጋ፣ ደምቢ ዶሎ፣ መቅደላ አምባ፣ ደባርቅ፣ እንጅባራ እና ወራቤ) የግንባታ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልግ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማሟላት በ2008 ዓ.ም በሁለተኛው ሩብ ዓመት ቢታቀድም ይህ ኦዲት እስከተከጠናቀቀበት ህዳር 2009 ዓ.ም ድረስ አለመሟላቱ፣
- አስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን ተቀብለው ማስተማር ሲጀምሩ የሚያስፈልጋቸውን የመጠጥና የጽዳት ውሃ በ2008 ዓ.ም በአራተኛው ሩብ ዓመት 50% ለማሟላት ቢታቀድም ለጂንካ፣ ቦንጋና ወራቤ ዩኒቨርሲቲዎች ለመጠጥ ውሃ ጥናት ውል ክፍያ እንዲሁም ለራያ እና ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲዎች የውሃ መስመር ማስገቢያ ግምት ክፍያ የተፈፀመ መሆኑንና ለእንጅባራ፣ መካነሰላም፣ ሰላሌ፣ ደንቢዶሎ፣ ቀብሪደሃር እና ደባርቅ ገና ሂደቱ ያልተጀመረ መሆኑ ኦዲቱ እስከ ተከጠናቀቀበት ህዳር 2009 ዓ.ም ድረስ ለሁሉም ሳይቶች ውሃ አለመሟላቱ፣
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ የአንደኛው ምዕራፍ የሕንፃና መሠረተ ልማት ግንባታ ሥራ ለማስጀመር መከናወን የሚገባቸው የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች (ወደ ግንባታ ሳይቶች የሚያስገባው መንገድ እና የግንባታ

ሳይቶች የውስጥ ለውስጥ መንገድ ከሶስተኛው ሩብ ዓመት 2008 ዓ.ም በፊት መሰራት ሲገባቸው በእያንዳንዱ ሳይቶች ከታሰበው ጊዜ ከሶስት ወራት በላይ ዘግይቶ የተሰራ ሲሆን የግንባታ ግብዓት ዕቃዎች ማስቀመጫ መጋዘኖች፣ የጥበቃ ሰራተኞች መቆጣጠሪያ ማማና ማረፊያ ቤት ግንባታዎች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ህዳር 2009 ዓ.ም አለመሰራታቸው)፣

- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በ2008 ዓ.ም በሁለተኛው ሩብ ዓመት እንደሚጀመር ማስፈፀሚያ እቅዱ ላይ ቢገለጸም ዘግይቶ በሰኔ /2008 ዓ.ም (በአራተኛ ሩብ ዓመት) መጨረሻ አካባቢ መጀመሩ፣
- በ2008 በጀት ዓመት በሁለተኛው ሩብ ዓመት የግንባታ ግብዓት ግዢ 100% ለማከናወን እና የግንባታ ግብዓት ስርጭት 30% በሁለተኛው፣ 65% በሶስተኛው እና 100% በአራተኛው ሩብ ዓመት ለማከናወን ተከልሶ በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ ቢገለጽም የተለያዩ ሚሊ ሜትር ብረቶች ለመግዛት ከአቅራቢ ድርጅቶቹ ጋር ውል የተገባው በየካቲት 21, 2008 ዓ.ም (በሶስተኛው ሩብ ዓመት)፣ ባለ 6 እና 8 ብረቶች እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም (በአራተኛው ሩብ ዓመት) እንዲሁም ሲሚንቶ እስከ መጋቢት 2008 ዓ.ም (በሶስተኛው ሩብ ዓመት) ድረስ ግዢዎች ያልተከናወኑ እና ስርጭቱም ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በአስራ አንዱቹም ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ሳይቶች የሚገኙ ተቋራጮች የግንባታውን ሂደት የሚያሳየውን ዋና የትግበራ መርሃ ግብር (Master Schedule) በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ ያላቀረቡ እና እስከ ህዳር 22/2009 ዓ.ም አማካሪ ድርጅቶቹና በትምህርት ሚኒስቴር የሚገኘው ዋናው የፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋናውን እና የተከለሰውን የትግበራ መርሃ ግብር ያላጸደቁ መሆኑ፣
- ማስፈፀሚያ እቅዱ ላይ የግንባታው ስታንዳርድ እና ዝርዝር ዲዛይን (Standard & Detail Design) በ2008 ዓ.ም በአንደኛው ሩብ ዓመት (ከሀምሌ2007-መስከረም 2008) እንደሚጠናቀቅ ቢገለፅም ስታንዳርድ ዲዛይኑ ያለቀው በሰኔ 2008 ዓ.ም መሆኑ እንዲሁም የዝርዝር ዲዛይን ስራ (የዲዛይን ማጣጣም ስራ) እስከ ሕዳር 30/2009 ዓ.ም ድረስ አለመጠናቀቁ፣
- የአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በ2008 ዓ.ም በሁለተኛው ሩብ ዓመት (ጥቅምት-ታህሳስ 2008) እንደሚጀመር ቢታቀድም ዘግይቶ በሰኔ/2008 ዓ.ም መጨረሻ መጀመራቸው፣

- የትምህርት መሳሪያዎች ግዥ በ2008 በጀት ዓመት ሌተር ኦፍ ክሬዲት (Letter of Credit) በመክፈት ማለትም ስታንዳርድና እስፔሲፊኬሽን ማዘጋጀት፣ የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀትና ጨረታውን አየር ላይ በማዋል፣ አሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶችን የመለየት ስራ ማከናወን እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል የመፈራረም ስራዎች እንደሚጠናቀቁ ቢገለጽም እስከ መጋቢት 30/2008 ዓ.ም ድረስ ለትምህርት መሣሪያዎች ግዢ ለመፈፀም የሚያስችል የመነሻ ስፔሲፊኬሽንና ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ በዩኒቨርስቲ ባለሙያዎች እየዳበረ እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም እስከ ታህሳስ/2009 ዓ.ም ግዥ ያልተፈጸመ መሆኑ፣
- የተፈጥሮ ሣይንስ የላብራቶሪ መሣሪያዎችና የማጣቀሻ መፃሃፍት ግዢ፣ የላብራቶሪ ፈርኒቸር፣ የፈርኒቸር፣ የምግብ ማብስያና ማቅረቢያ ዕቃዎች እሰከ ታህሳስ 2009 ዓ.ም ግዥ ያልተፈጸመ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ዋናው የግንባታ ሂደቱ በእቅዱ መሰረት እየሄደ እንዳልሆነ ለአብነት፡-
    - ➢ በወራቤ ዩኒቨርሲቲ በግንቦት/ሰኔ 2008 ዓ.ም የፋይናንሽያል ሥራ 5.01% ለመስራት ቢታቀድም የተሰራው 1.71% መሆኑ እና እስከ ሐምሌ 30/ 2008 ዓ.ም በአጠቃላይ 10% መሰራት ሲገባው የተሰራው ግን 0.87% የዕቅዱን 9 ከመቶ ብቻ መሆኑ፣
    - ➢ በራያ ዩኒቨርሲቲ ግንባታው በመስከረም 2009 ዓ.ም ለመስራት የታቀደው 9% ቢሆንም የተሰራው 3.3% የዕቅዱን 37 ከመቶ ብቻ መሆኑ፣
    - ➢ በደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ በሐምሌ 2008 ዓ.ም ለመስራት የታቀደው 8% ቢሆንም የተሰራው 2.73% የዕቅዱን 34 ከመቶ ብቻ መሆኑ እንዲሁም
    - ➢ በመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ በሐምሌ 2008 ዓ.ም ለመስራት የታቀደው 24.58% ቢሆንም የተሰራው 0.79% የዕቅዱን 3 ከመቶ ብቻ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሰው መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የስታንዳርድ ዲዛይን ዋጋ በድርድር የተደረሰበት ሲሆን ይህም የመጨረሻው ዝቅተኛ ዋጋ እንደሆነ ታምኖበት የተወሰነ መሆኑና የበጀት ግምት የተወሰደው ከአስሩ እና አስራ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ በመውሰድ በአስራ አንዱ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ የሕንፃዎችን

ዝርዝር ዲዛይኖች ጨምሮ ዋና አማካሪው እንዲሰራ በመወሰኑ ዋጋው ከተመደበው በጀት ከፍ ያለ መሆኑን፣ የዩኒቨርሲቲ ግንባታ ሳይቶች የቦታ ርክክብ እንዳልዘገየ፣ በግንባታው ምክንያት ከቦታው ለሚነሱ ለተነሽዎች የካሳ ግምቱ ስራ ዋጋው የተጋነነ በመሆኑ መዘግየቱን እንዲሁም የኦዳ ቡልቱም የግንባታ ሳይት ለተነሽዎች እስከ ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም የካሳ ክፍያ ባለመፈጸሙ ግንባታው እንዳልተጀመረ እንዲሁም ከኦዳቡልቱም በስተቀር ለሌሎች ፕሮጀክት ሳይቶች የሰው ሃይል እንደተሟላላቸው ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ እና በመውጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

39. በተጨማሪም የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት በየካቲት 30/2009 ዓ.ም የመጀመሪያው የምዕራፍ ግንባታ መጠናቀቅ እንደነበረበት እና የግንባታው ሂደት ያለበትን ሁኔታ እስከ የካቲት 25/2009 ዓ.ም ድረስ የተደረገው ግምገማና ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ ማስረጃ በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገው ውይይት ላይ ባቀረቡት ሰንጠረዥ ላይ መጠናቀቅ ከሚገባቸው ጊዜ መዘግየቱን ነገር ግን በመስከረም ወር ለሚደረገው ቅበላ ለማድረስ ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

| ተ.ቁ | ዩኒቨርሲቲ | ግንባታው ያለበት ደረጃ በፐርሰንት |
|---|---|---|
| 1. | ደባርቅ | 69.36% |
| 2. | እንጅባራ | 66.29% |
| 3. | መቅደላ አምባ<br>• መካነሰላም | 60% |
| | • ቱሉ አዋሊያ | 55% |
| 4. | ሰላሌ | 48.68% |
| 5. | ደምቢ ዶሎ | 75.44% |
| 6. | ራያ | 67.48% |
| 7. | ቦንጋ | 55.36% |
| 8. | ወራቤ | 64.39% |
| 9. | ጂንካ | 78.02% |
| 10. | ቀብሪ ደሃር | 37.73% |
| 11. | ኦዳቡልቱም | ግንባታው እስከ 25/06/09 ዓ.ም አልተጀመረም፡፡ |

40. አስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ኘሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ባለመሆኑ ግንባታው እንዲጓተት አድርጓል፡፡ በመሆኑም ግንባታው በዘገየ ቁጥር መንግስት ለተጨማሪ ወጪ እንደሚዳረግ እና አስራ አንዱም ዩኒቨርሲቲዎች የመጀመሪያ የግንባታ ምዕራፍ ተጠናቆ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማስጀመር የሚገለግሉ

ግብዓቶች ተሟልተው በ2010 ዓ.ም እያንዳንዳቸው 1500 በድምሩ 16500 ተማሪዎች ተቀብሎ ትምህርት የማስጀመር እቅዱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

**በባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፤**

41. ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክቱ እቅድ አፈፃፀም ላይ ያላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ በቅንጅት መስራት አለባቸው፡፡

42. አስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ዕቅድ ሊተገበር የሚችል (Realistic) እና የመማር መስተማር ስራውን በተቀመጠው እቅድ መሰረት ለማስጀመር እንዲረዳ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክቱ እቅድ አፈፃፀም ላይ ያላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ

43. በቅንጅት ባለመሰራቱ፡-

- በየግንባታ ሳይቱ የግንባታ ግብዓት ማስቀመጫ መጋዘን ለማስራት የሚያስፈልገው ፕላንና የስራ ዝርዝር በአማካሪ ድርጅት እንዲዘጋጅ ተደርጎ ግንባታውን የሚያከናውኑ የስራ ተቋራጮች በጨረታ አወዳድረው ውጤቱን እንዲልኩ ለከተማና ለዞን አስተዳደሮች ትምህርት ሚኒስቴር ጥያቄ ቢያቀርብም ምላሽ ያልሰጡ መሆኑን፣ ላላስፈላጊ የመጋዘን ክራይ ወጪ እየተዳረጉ እና ከዲዛይን ችግሮች ጋር በተያያዘ ከተቋራጮች ለሚቀርበው ጥያቄ በአማካሪ እና በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ወቅታዊ መፍትሄ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ከክልል፣ ዞንና ከወረዳ ጽ/ቤቶችና ከተቋራጭ ድርጅቶች ጋር ያለው ቅንጅታዊ አስራር ደካማ መሆኑ ለምሳሌ ለባለይዞታዎች የሚፈጸም ካሳ በወቅቱ ጥናቱ ያልተከናወነና ጥናቱም መያዝ ያለባቸውን ጉዳዮች ሁሉንም አሟልቶ የማያካትት መሆኑ፣ የተጋነነ ግምት እና ያልተጣራ ሰነድ በተደጋጋሚ የሚቀርብ መሆኑና ክፍያው በቶሎ የማይፈፀም መሆኑ፣
- ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት እና ከየክልል ውሃ ሀብት ቢሮዎች ጋር ያለው ግንኙነት ደካማ መሆኑ የኤሌክትሪክ ኃይል እና የውሃ አቅርቦት አገልግሎቶች ለዩኒቨርሲቲ ግንባታ ሳይቶች በወቅቱ ያልገባላቸው እና እስከ ህዳር 30/2009 ዓ.ም ድረስ አገልግሎቱን ያላገኙ መሆናቸው፣
- በየሳይቱ ያሉ የፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎች ፕሮጀክት ፅ/ቤቶቹ ለሚያነሷቸው ችግሮችና ጉዳዮች የዞን አስተዳደሮች እና የከተማ ከንቲባዎች ፈጣን ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን፣ እና በትምህርት ሚኒስቴር ካለው ዋናው ፕሮጀክት ፅ/ቤት

ጋር ባለው የሥራ ግንኙነት ለመጥቀስ ያህል ባለሙያ እጥረት መኖሩን፣ የሰራተኛ መገልገያዎች እና የቢሮ መገልገያ ጠረጴዛ፣ ወንበሮች፣ ኮምፒውተሮች፣ ስልኮች፣ ፋክስ ማሽኖች እንዲሁም ልሎች እቃዎች ከማሟላት እንዲሁም የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ከማቅረብ እና ምላሽ ከመስጠት አንፃር ያለው የስራ ግንኙነት የላላ መሆኑን መግለጻቸው፣

በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የወራቤ፣ እንጅባራ እና ራያ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች፣ አማካሪ ድርጅት ኃላፊዎች፣ የግንባታ ስራ ተቋራጮች፣ የዞን እና ከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች እንዲሁም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቆጣጣሪ መሐንዲስ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ከሰጡት መልስ፣ ከተከለሱ መረጃዎች እና በመስክ ጉብኝት ወቅት በተገኘው መረጃ መሠረት ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. ስለሁኔታው የትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኤሌክትሪክ ኃይል እና የውሃ አገልግሎት በተወሰኑ የግንባታ ሳይቶች በወቅቱ እንዳላገኙ እና የኦዲት አስተያየቱን በግብዓትነት እንደሚጠቀሙ ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ እና በመዉጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

45. የአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ሰራን አስመልክቶ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክቱ እቅድ አፈፃጸም ላይ ያላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ የዩኒቨርሲቲዎቹ ግንባታ ስራ እንዲጓተት ከማድረጉም በላይ ተቋሞቹ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማስጀመር የታቀደውን ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

## 2.2. የአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በእቅዱ መሠረት በመተግበር የተማሪ ቅበላ ሂደቱ በተቀመጠለት የዕቅድ መርሃ ግብር መሰረት መከናወኑን፤

**ሊያጋጥሙ የሚችሉ የግንባታ ሥጋቶችን (Risks) ማጥናትና ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግን በተመለከተ**

46. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታው ሂደት ከመጀመሩ በፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን (Risks) በቅድሚያ በማጥናትና በመለየት እንዲሁም ግንባታዎቹ ተጠናቀው የመማር ማስተማሩ ሂደት ሲጀምር በዘላቂነት እንዳይቀጥል ሊያደርጉ

የሚችሉ ሥጋቶች እንዳይከሰቱ በቅድሚያ ተለይተው ቅድመ ጥንቃቄና ዝግጅት ሊደረግ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጂ የአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክት ግንባታዎች ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ በትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን ለይቶ ያላስቀመጠ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው ከታዩት የወራቤ፣ እንጅባራ እና ራያ ዩኒቨርሲቲ ሳይቶች

- ለግንባታ ስራው እንዲሁም ለተማሪዎችም መጠጥና ለጽዳት ስራ የሚያገለግል ቀጣይነታ ያለው የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ለማስቻል የተጠና ጥናት አለመኖሩን፣
- ከኤሌክትሪክ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ተቋራጮቹ ስጋቶቻቸው ለይተው በማስቀመጥ በተደጋጋሚ ለትምህርት ሚኒስቴር ማሳወቃቸውና ነገር ግን ችግራቸው አለመፈታቱ፣

በኦዲቱ ወቅት የፕሮጀክት ግንባታ ሂደቶችን የሚያስረዱ መረጃዎችን በመከለስ እና ግንባታዎቹ በአካል በታዩበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. ስለጉዳዩ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የምህንድስና ጉዳዮች ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ፣ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች፣ አማካሪ ድርጅት ኃላፊዎች፣ የግንባታ ስራ ተቋራጮች፣ የዞን እና ከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች እንዲሁም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቆጣጣሪ መሐንዲስ ተጠይቀው ለግንባታ የሚያገለግሉ ድንጋይ፣ አሸዋ፣ ጠጠር እና ሌሎችም ግብዓቶች ጋር በተያያዘ የሚገኙበት ሁኔታ እና ቦታዎች መለየታቸው፣ ከውሃ ጋር በተያያዘ የአዋጭነት ጥናቶች እንዲጠኑ እና ውል ከክልሎች ውሃ ቢሮዎች ጋር እንዲገባ መደረጉን እንዲሁም አንዳንድ ከተሞች የውሃ እጥረት ያላቸው ቢሆንም የውሃ አገልግሎት እንዲያገኙ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም እነዚህ ስራዎች ግንባታው ከመጀመሩ በፊት መሰራት የነበረባቸው ሲሆን ችግሮቹን ለመፍታት እየተሰሩ ያሉ ነገሮች አዝጋሚ መሆናቸው በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

49. ስለሁኔታው የትምህርት ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች የክዋኔ ኦዲት ግኝቱን እንደግብዓትነት እንደሚጠቀሙበት ለረቂቅ ሪፖርቱ እና በመዉጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

50. የግንባታዎች ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ በትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን ለይቶ ባለማስቀመጡ የግንባታ ስራውን ከማጓተቱ በተጨማሪ በቀጣይነት

አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የውሃ እና የኤልክትሪክ አገልግሎት እጥረት ጉዳይ በመማር ማስተማሩ ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡

**የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች በሰው ሃይልና በቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች መደራጀታቸውን በተመለከተ፣**

51. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ኘሮጀክት ግንባታን የሚያስፈጽሙ ጽ/ቤቶች በትምህርት ሚኒስቴርና በየግንባታ ፕሮጀክቱ ሳይቶች ላይ ሊቋቋሙ እና በተገቢው ግብዓቶች ሊደራጁ ይገባል፡፡ አሥራ አንዱም የግንባታ ኘሮጀክት ጽ/ቤቶች የሥራ ኃላፊነት እና ተግባራት በዝርዝር ሊገለጽ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ በትምህርት ሚኒስቴር በተቋቋመው ፕሮጀክት ጽ/ቤት በአንደኛው ሩብ ዓመት ለማሟላትና በሳይት ላይ ላሉት በሁለተኛው ሩብ ዓመት በሁለት ወራት ውስጥ ለማሟላት በ2008 ዓ.ም ተከልሶ በተዘጋጀው እቅድ ላይ ቢታቀድም በዋናው ፕሮጀክት ፅ/ቤት እና በሳይት የሚገኙት ፅ/ቤቶች በሰው ሃይልና በቢሮ መገልገያ እቃዎች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አልተሟላላቸውም፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ከዋናው የፕሮጀክት ጽ/ቤት ጋር የሚኖራቸው የስራ ግንኙነት የሚገልጽ የስራ ኃላፊነትና ዝርዝር ተግባራት በሰነድ ተዘጋጅቶ ያልተሰጣቸው መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. ስለጉዳዩ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የወራቤ፣ የእንጂባራ እና የራያ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች ተጠይቀው የሰው ኃይል እና የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች (ኮምፒውተር፣ ወንበር፣ ስልክ፣ ፋክስ ማሽኖች እና የመሳሰሉት) ያልተሟሉ መሆኑን እንዲሁም ተሽከርካሪ መኪና ባለመኖሩ የግንባታ ሳይቶችን አምስት ኪሎ ሜትር ያህል በእግር በመጓዝ እንደሚቆጣጠሩ እና ፕሮጀክት ጽ/ቤቶቹ ከዋናው ፕሮጀክት ጽ/ቤት ጋር ያላቸው የስራ ግንኙነት፣ የሚጠበቅባቸው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በጽሁፍ እንዳልተገለጸላቸው በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ እንዲሁም በመስክ ኦዲት ወቅት በአካል ለማየት ተችሏል፡፡

54. ስለጉዳዩ የትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊዎች ተጠይቀው ሁሉም ሳይቶች ቢሮ፣ መጋዘንና የሰው ሃይል ተሟልቶላቸው ወደ ስራ የገቡ መሆኑን፣ የቢሮ ቁሳቁስ በከፊል ያልተሟላላቸው መሆኑን ይህም በግዥ ሂደት ባጋጠመው ችግር በመሆኑ ምክንያት ሲሆን፣ ለዋናው ፕሮጀክት ፅ/ቤት የመንግስት አቅም በፈቀደው መጠን ከሞላ ጎደል

የተሟላ እንደሆነና በተጨማሪም በኦዲቱ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ በመውሰድ እንደአስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወሰድ ለክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርቱ እና በመዉጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ግኝቱን እንደግብዓትነት እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል፡፡

55. የፕሮጀክት ጽ/ቤቶችን በሰው ሃይል እና በቢሮ መገልገያ መሳሪያዎችና እቃዎች አለመደራጀታቸው እና በየጽ/ቤቶቹ የሚሰሩ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት እንዲደርሳቸው አለመደረጉ የግንባታ ስራውን በሚፈለገው ደረጃ ለመቆጣጠርና ለመከታተል እንቅፋት እንዲሁም ግንባታዎቹ ጥራታቸውን ጠብቀው እንዳይከናወኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ግንባታውን አስመልክቶ የአካባቢና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት የተከናወነ መሆኑን በተመለከተ፣**

56. ሚኒስቴር መ/ቤቱ (ፕሮጀክት ጽ/ቤቱን ጨምሮ) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉ መስተዳደር እና ሌሎች የግንባታ ፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለአካባቢው ህብረተሰብ የዩኒቨርሲቲዎቹ ጥቅም የግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይት ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የዩኒቨርሲዎቹ ግንባታ በሚገነቡበት ቦታ ሊከሰት የሚችለው የአካባቢና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት እና ለመልሶ ማቋቋሚያ መርሀ ግብር ጥናት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

57. ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲዎቹ ተገንብተው ሲጠናቀቁ ለአካባቢው ህብረተሰብ እና ለሀገር ያለውን ፋይዳ እንዲሁም የግንባታ ፕሮጀክቶቹ አስፈላጊነት በተመለከተ የግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይት ያልተደረገ መሆኑ፣ የዩኒቨርሲቲዎቹ ግንባታ በፕሮጀክት ትግበራ ወቅትም ሆነ ሥራ ከጀመሩ በኋላ በአካባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ተጽዕኖ የግምገማ ጥናት እና ለመልሶ ማቋቋሚያ መርሃ ግብር ጥናት ያልተዘጋጀ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. ስለጉዳዩ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የወራቤ፣ እንጅባራ እና ራያ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስራ አስኪያጆች ተጠይቀው የግንባታ ፕሮጀክቶቹን አስመልክቶ ለአከባቢው ህብረተስብ ያለውን ፋይዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንዳልተሰራና ግንባታው በአካባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ላይ ያለውን ተጽዕኖ እንዲሁም መልሶ ማቋቋሚያ መርሃ ግብር በጥናት ያልተደገፈ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

59. ስለሁኔታው የትምህርት ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በግንባታ ቦታ ርክክብ ወቅት ስለ ካሳ አከፋፈሉ፣ ዩኒቨርሲቲው ቢገነባ የሚኖረው አከባቢያዊ ጠቀሜታ ቦታውን ለርክክብ የሄደው ቡድን ከወረዳው ወይም ከከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች ጋር ተገቢው ውይይት መደረጉን ለረቂቅ ሪፖርቱ እና በመዉጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ግኝቱን እንደግብዓትነት እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ተገቢው ውይይት መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ እና የአካባቢና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማን በተመለከተ መከናወኑን ምላሽ አልሰጡም፡፡

60. የአስራ አንዱ የዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክቶች የአካባቢው ህብረተሰብ ከልማቱ ተጠቃሚ ስለመሆኑ እና ለሀገር እድገትና ብልጽግና ያለውን ፋይዳ በግልጽ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ባለመሰራቱ እንዲሁም ግንባታው በአካባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ላይ ያለውን ተጽዕኖ እና መልሶ ማቋቋሚያ መርሃግብር በጥናት ባለመደገፉ ህብረተሰቡ የፕሮጀክት ግንባታዎቹን እንዲሁም ግንባታዎቹም ሲጠናቀቁ ተቋሞቹን በባለቤትነት ስሜት የመንከባከብ እና የመጠበቅ ድርሻውን እንዳይወጣ ያደርጋል፡፡

**በግንባታው ምክንያት ለሚነሱ ተነሺዎች የተያዘው በጀት በበቂ ጥናት ላይ አለመመስረቱ፣ የሚከፈል የካሳ ክፍያ እና የካሳ ክፍያ መዘግየቱን በተመለከተ፤**

61. ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ምክንያት ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ካሣ ሊከፈል ይገባል፡፡ ካሳ የተከፈላቸው ተነሺዎች የካሣ ክፍያ ከተፈፀመላቸው በኋላ ከቦታቸው በተቀመጠው ቀነ ገደብ መነሳት አለባቸው፡፡

62. ይሁን እንጂ ለአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ምክንያት ከግንባታ ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ካሣ እንዳልተከፈላቸው እና ካሳ የተከፈላቸውም የአካባቢው ነዋሪዎች ከቦታው በተቀመጠው ቀነ ገደብ እንዳልተነሱ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከግንባታ ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ካሣ ባለመከፈሉ እና ካሳ የተከፈላቸውም የአካባቢ ነዋሪዎች ከቦታው በተቀመጠው ቀነ ገደብ ባለመነሳታቸው፡-


**ለተነሽዎች የካሳ ክፍያ በጀት በበቂ ጥናት ላይ መመስረቱን በተመለከተ፡**

- ከአስሩ እና አስራ ሶስቱ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ከተወሰደው ተሞክሮ በጥቅል ማስገባቱ ለተነሽዎች የካሳ ክፍያው በአግባቡ እንዳይከፈል አድርጎት ነበር፡፡ ይህ በዚህ በአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጄክት ግንባታ እንዳይከሰት በባለይዞታዎቹ የግል አካዉንታቸው መግባት እንደሚገባ በትምህርት ሚኒስቴር በ07/08/2008 ዓ.ም ያወጣው መመሪያ ይገልጻል፡፡
- ይሁን እንጂ በራያ ዩንቨርሲቲ ግንባታ ምክንያት ለሚነሱ ግለሰቦች ብር 70,471,773.01 ለ383 ባለይዞታዎች በግል አካዉንታቸው መግባት ሲገባው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያወጣው መመሪያ ተጥሶ በጥቅሉ በደደቢት ብድርና ቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ እንዲገባ መደረጉ እና እስከ ህዳር 29/2009 ዓ.ም ድረስ ለካሳ የተከፈለው ገንዘብ እንዲወራረድ እና መክፈል ያልተቻለው በጥሬ ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ አለመደረጉ ታውቋል፡፡ እንዲሁም በካሳ ተከፋዮች ዝርዝር የቀረበው የካሳ ክፍያ ዝርዝር ድምርና ክልሉ በደብዳቤ እንዲከፈል በጠየቀው እና በተላከው ጠቅላላ ተከፋይ መካከል የብር 703,104.74 ብልጫ የተጠየቀው እና የተላከው (ወደ ብድርና ቁጠባው ሂሳብ የገባው) እንዳለው እየታወቀ በደደቢት ብድርና ቁጠባ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ እንዲገባ መደረጉን ታውቋል፡፡
- በሰላሌ፣ በቦንጋ እና በእንጅባራ ዩንቨርሲቲዎች በግንባታ ምክንያት ለሚነሱ ግለሰቦች እንደቅደም ተከተላቸው ብር 6,887,668.00 ለ48፣ ብር 570,422.73 ለ4 እና ብር 1,995,905.28 ለ33 ባለይዞታዎች የሚሆን የካሳ ክፍያ ገንዘብ በግል አካዉንታቸው መግባት ሲገባው ትምህርት ሚኒስቴር በ07/08/2008 ዓ.ም ያወጣው መመሪያ ተጥሶ በጥቅሉ በፍቼ ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት መምሪያ ሂሳብ ቁጥር በሰኔ 28/2008 ዓ.ም፣ በከፋ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ግዥ ክፍያና ንብረት አስተዳደር ሂሳብ ቁጥር በሰኔ 28/2009 ዓ.ም እና በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ባንክ ሂሳብ አካውንት ውስጥ በሰኔ 25/2009 ዓ.ም እንዲገባ መደረጉ እና እስከ ህዳር 29/2009 ዓ.ም ድረስ ገንዘቡ ያልተወራረደ መሆኑ፣
- የራያ እና የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ሳይቶች የካሳ ክፍያ ገማች ኮሚቴ ቃለ ጉባዔ በዞን አስተዳደር፣ በፕሮጀክት ጽ/ቤት እና በከተማው ከንቲባ

ጽ/ቤት አለመገኘቱን እና ለትምህርት ሚኒስቴር እንዲከፈል በተላከው ሰነድ ውስጥም ያልተያያዙ መሆናቸው፣

- ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይቶች የካሳ ክፍያ ጥናት ለመስራት የተቋቋሙት የካሳ ገማች ኮሚቴዎች ስብጥር ከየትኛው ተቋም ወይም መስሪያ ቤት እንደተመደቡ እና የስራ ድርሻቸው አለመገለጹ፣ ባለይዞታዎቹ የካሣ ክፍያ ከተፈፀመላቸው በኋላ ከቦታቸው የሚነሱበት ቀን ገደብ ተገልጾ ደብዳቤ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- ትምህርት ሚኒስቴር አንዳንድ ቦታዎች ላይ የካሳ አገማመቱ ሁኔታ የተጋነነ ነው በመባሉ ስለሁኔታው ለማስረዳት ብዙ ምልልሶች መኖራቸው ለምሳሌ፡ ደምቢ ዶሎ ብዙ ምልልስ የነበረ መሆኑንና በኋላም ከ200 ሄክታር ቦታ ግማሹን ብቻ (100 ሄክታር) መከፈሉን፣
- ደባርቅ ላይ በመጀመሪያ ከካሳ ነፃ ቦታ ነው ተብሎ የነበረ መሆኑና በኋላ ግን በስህተት ነው ካሳ ተከፋዮች አሉ ተብሎ ግንባታው ከተጀመረ በኋላ የይከፈለን ጥያቄ መነሳቱን፣ ደምቢ ዶሎ ላይ ማረሚያ ቤት የመንግስት ነው ካሳ አይከፈለውም ተብሎ የነበረ ሲሆን 13 ሚሊዮን ብር የይከፈለን በደብዳቤ ጥያቄ መቅረቡን እንዲሁም ከክልል የሚላኩ የካሳ ተከፋይ መረጃዎች የተሳሳተ በመሆናቸው የተከፋዮቹ ሂሳብ ቁጥርና ስም ስህተት ተፈጥሮ ባንክ ስለመመለሳቸው የክፍያ የስም እና የሂሳብ ቁጥሮች በርካታ ስርዝ ድልዞች መኖራቸው፡፡

- ለካሳ ክፍያ የተያዘው በጀት በበቂ ጥናት ላይ ባለመመስረቱ ከዚህ በታች በምስል 2 እና በሰንጠረዥ 3 ታይቷል፡፡




<u>ምስል 2</u>. ለካሳ ክፍያ የተያዘው በጀት ከተከፈለው ጋር ማነጻጸሪያ፡፡

| | ለካሳ ክፍያ የተያዘ በጀት | የተከፈለ ብር | በልዩነት ከበጀት በላይ ብር |
|---|---|---|---|
| የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይት (ለ100 ሄክታር መሬት) | 20,000,000.00 | 69,893,352.10 | 49,893,352.10 |
| የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይት ለ200 ሄክታር መሬት (137 ሄክታር መሬት መሆኑን ለቀሪው 63 ሄክታር መሬት ትምህርት ሚኒስቴር በጀት የለም በማለቱ የቦታ ርክክብ ያልተደረገ መሆኑን፣) | 20,000,000.00 | 17,788,843.69 | |
| የራያ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይት | 20,000,000.00 | 70,471,773.01 | 50,471,773.01 |
| የመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይት | 20,000,000.00 | 27,685,359.05 | 7,685,359.05 |
| የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይት | 20,000,000.00 | 29,232,049.31 | 9,232,049.31 |

<u>ሰንጠረዥ3.</u> ለካሳ ክፍያ የተያዘው በጀት ከተከፈለው ጋር ማነጻጸሪያ፡፡

## ለተነሽዎች ካሳ በህግና መመሪያ መሰረት አለመከፈሉን፤

- በራያ ዩንቨርሲቲ የግንባታ ፕሮጀክት ከ35 ካሳ ተከፋዮች በላይ ሂሳባቸው እንደገና መሰራት አለበት፣ የመንግስት ሰራተኛ ናችሁ፣ ከዚህ ወረዳ ለቃችኋል

እና የዚህ ወረዳ ነዋሪ አይደላችሁም በሚልና በሌሎች ምክንያቶች መጀመሪያ ክልሉ አጥንቶ ካጸደቀው ብር 7,347,757.30 የገንዘብ መጠን ብር 4,049,779.00 በመቀነስ ብር 3,279,978.30 ለካሳ ተከፋዮች እንዲከፈል መታዘዙን እስከ ህዳር 30/2008 ዓ.ም ድረስ በካሳ አከፋፈሉ በርካታ ቅሬታዎች መኖራቸውንና ትምህርት ሚኒስቴርም ለጉዳዩ መፍትሄ እንዲያገኝ ያላደረገ መሆኑን እንዲሁም መጀመሪያ ካሳ ክፍያ ጥናቱ ውስጥ ያልተካተቱ ስድስት(6) ተነሽዎች ካሳ ብር 399,706.32 እንዲከፈላቸው መደረጉን፡፡

- በመቅደላ አምባ የግንባታ ሳይት ብር 3,210,218.24 ብር ተከፍሏል ቢባልም የክፍያ ሰነዱ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፣
- በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ሳይት በተመሳሳይ ስም በተመሳሳይ አካውንት ቁጥር 1000128557917 ብር 79,938.00 ሁለት ጊዜ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን፣ የባንክ አካውንት ቁጥር 21650105072 በእስክሪብቶ ተሰርዞ ብር 97,000.00 የተከፈለ መሆኑን፣ የመጀመሪያ የባንክ አካውንት ቁጥር 210501050721 ተሰርዞ በሌላ አካውንት ቁጥር 1000011474601 በእስክሪብቶ ተቀይሮ ክፍያ እንዲፈጸም መደረጉን እንዲሁም የካሳ ግምቱም ትክክል ስለመሆኑ በባለይዞታዎች ፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ የካሳ ክፍያ ጥናቱ ላይ እንዲከፈላቸው የቀረበው ለ121 ግለሰቦች ብር 14,194,669.50 ሲሆን ለ81 ግለሰቦች ብር 8,062,072.00 የተከፈላቸውና ሂሳቡም ያልተወራረደ መሆኑ፣
- በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ሳይት የአባት፣ የተከፋይ እና የአያት ስሞች በጥናቱ ላይ በትክክለኛው ያለመፃፍ (ለምሳሌ አቶ ኬሮ አለሙ ሚሺ የአያታቸው ስም ሚሺ የሚለውን በእስክሪብቶ ተሰርዞ ገብሬ ተብሎ ክፍያ መፈፀሙ፣) ወ/ሮ እመቤት ወንዳፍራሽ ብዙነህ የባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው V03501009381 በእስክሪብቶ ተጽፎ ብር 120,022.60 እንዲከፈላቸው መደረጉ፣
- የወራቤ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ሳይት የካሳ ክፍያ ተከፋዮች ስም ዝርዝር ቅፅ ላይ ስማቸውንና አካውንት ቁጥራቸውን ብቻ የተገለጸ ሲሆን የተከፈላቸው የገንዘብ መጠን የማይገልጽ እና ስለመቀበላቸው በፊርማ ያላረጋገጡ እንዲሁም የተከፋዮች አካውንት ቁጥርና ስም የተሰረዘ መኖሩን፣

**ለተነሽዎች ካሳ ክፍያ መዘግየቱን፤**

- ለግንባታ ፕሮጀክቶቹ የቦታ ርክክብ ተጠናቆ ለግንባታ ዝግጁ የሆኑ ቦታዎች በቁጥር 11 ቦታዎች እያንዳንዱ ሳይት ላይ በአማካይ 200 ሄክታርና በብር 20 ሚልዮን በጀት በአንደኛው ሩብ ዓመት 2008 ዓ.ም በ30 ቀናት ውስጥ ለማከናወን ቢታቀድም፡-
  - የቦንጋ ዩኒቨርስቲ ግንባታ ሳይት የመጀመሪያው የካሳ ግምት ተሰርቶ ለትምህርት ሚኒስቴር የተላከው በሶስተኛው ሩብ አመት በቀን 24/05/2008 ዓ.ም ሲሆን ጥናቱ ተጠናቆ በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ ለሚኒስቴሩ የተላከበት ቀን 15/07/08 ዓ.ም (በሶስተኛው ሩብ ዓመት) መሆኑ፣
  - የእንጅባራ ዩኒቨርስቲ ግንባታ ሳይት የመጀመሪያው ካሳ ክፍያ የተሠራው በሁለተኛው ሩብ ዓመት በቀን 15/02/2008 ዓ.ም ሲሆን በድጋሚ ተሠርቶ ለትምህት ሚኒስቴር የተላከው 23/07/2008 ዓ.ም (በሶስተኛው ሩብ ዓመት) ይህም ማለት ከዕቅዱ ከስድስት ወራት ዘግይቶ መሆኑን እንዲሁም
  - የጂንካ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ሳይት የካሳ ክፍያ ተጠናቆ ለትምህት ሚኒስቴር የተላከው በሶስተኛው ሩብ ዓመት በ19/07/2008 ዓ.ም ሲሆን በመጋቢት 16 /2008 ዓ.ም (በሶስተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ) የካሳ ክፍያው የተከናወነ መሆኑን፣
- የአዳ ቡልቱም ዩኒቨርስቲ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይት የካሣ ክፍያ ጥናቱ ተጠናቆ ክፍያ ባለመፈጸሙ ግንባታው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት እስከ ህዳር 30/2009 ዓ.ም ድረስ የግንባታ ስራ ያልተጀመረ መሆኑን፣
- የደባርቅ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ፕሮጀክት ሳይት ለካሳ ክፍያ የተያዘ በጀት ያልቀረበ መሆኑን፣
- በወራቤ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ሳይት የካሳ ክፍያ ከተፈፀመላቸው ከግንባታ ቦታው ያልተነሱ አስራ ሰባት(17) አባወራዎች ቤታቸው ሳይፈርስ እና በማሳቸው ላይ ሰብል ዘርተው የተቀመጡ መሆናቸው እንዲሁም ካሳ ክፍያ ያልተከፈላቸው እና ያልተነሱ ሁለት(2) አባወራዎች መኖራቸውን እንዲሁም ቁጥራቸው በትክክል የማይታወቅ አባወራዎች ካሳ ክፍያ ተፈጽሞላቸው ከተነሱ በኋላ ወደ ግንባታው ሳይቱ በድጋሚ እየገቡ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የወራቤ፣ እንጂባራ እና ራያ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች፣ አማካሪ ድርጅት ኃላፊዎች፣ የግንባታ ስራ ተቋራጮች፣ የዞን እና ከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች እንዲሁም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቆጣጣሪ መሐንዲስ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ እንዲሁም የፕሮጀክት ግንባታ ሂደቶችን የሚያስረዱ መረጃዎችን በመከለስ እና ግንባታዎቹ በኦዲት መስክ ጉብኝት ወቅት በአካል ለማየት ተችሏል፡፡

63. ስለጉዳዩ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የፋይንስና የሰው ሃይል አስተዳደር ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠይቀው ካሳ ክፍያው በደደቢት ብድርና ቁጠባ የባንክ ሂሳብ ቁጥር የገባበት ምክንያት የትምህርት ሚንስቴር የበላይ ስራ አመራር በወሰኑት መሰረት መሆኑን፣ የካሳ ክፍያ የማይገባቸው ሰዎች የነበሩ በመሆኑ የማጣራት ስራ ለመሰራት ስለሚገባ እና እስከ ህዳር 30/2008 ዓ.ም ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ እንዳልተወራረደ (ክፍያው በትክክል ስለመከፈሉ የሚያስረዱ ሰነዶች በፋይናንስ ክፍል መኖሩን) እና ገንዘቡ በደደቢት ብድርና ቁጠባ የባንክ ሂሳብ ቁጥር የሚገኝ መሆኑን፣

64. ስለሁኔታው የትምህርት ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የቦታ ርክክብ ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ እንደተከናወነና የካሳ ግምት ስራው እንደዘገየ ይህም የሆነው ግምቱ የተጋነነ በመሆኑ እንደሆነና እስካሁንም የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ እንዳልተከፈለ፣ ካሳ የተከፈላቸው ሰዎች ያልተነሱት የከተማው አስተዳደር ቦታ እስኪያመቻችላቸው መሆኑንና ሌሎችም ቦታዎች እንደዚህ ዓይነቶቹ ሁኔታዎች መኖራቸውና የግንባታው ስራ ሂደቱን እንዳላደናቀፉት እና የካሳ ክፍያ ሁኔታዎቹ በደንብ ካልታዩ ለኪራይ ሰብሳቢነት፣ ለመልካም አስዳደር ችግሮችና ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ስለሚችል ጉዳዮቹ ጥብቅ ክትትል እየተደረገባቸው እንደሆኑ ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሑፍ እና በመውጫ ስብሰባ ላይ በስጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ለሌሎች ከላይ ለተገለጹት ጉልህ ግኝቶች ምላሽ አልሰጡም፡፡

65. ለአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ምክንያት ከግንባታ ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ካሣ አለመከፈሉ መንግስት ለካሳ ክፍያ የመደበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል ከማድረጉም በላይ መንግስት ለአላስፈላጊ ወጪ እንዲዳረግ ያደርገዋል እንዲሁም ካሳ

የተከፈላቸውም የአካባቢው ነዋሪዎች ከቦታው እንዲነሱ ባለመደረጉ በየግንባታ ሂደቱን ሊያስተጓጉሉት ይችላሉ የሚል ስጋት አለ፡፡

**የውሃ እና የኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት አቅርቦትን በተመለከተ፣**

66. ለአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያገለግል የዉሃ፣ የኤሌክትሪክ ሀይል እና የቴሌኮም አገልግሎት አቅርቦቶች ግንባታው ከመጀመሩ በፊት ሊሟሉ ይገባል፡፡

67. በኦዲት ወቅት የዉሃ፣ የኤሌክትሪክ ሀይል እና የቴሌኮም አገልግሎት አቅርቦቶች ግንባታዎቹ ከመጀመራቸው በፊት ለአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ሳይቶች ያልተሟሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ሳይቶች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በ2008 በጀት ዓመት በሁለተኛው ሩብ ዓመት በአራት ወራት ውስጥ ለማሟላት በነሐሴ 2007 ዓ.ም በተዘጋጀው እቅድ እና በጥቅምት 2008 ዓ.ም ተከልሶ በተዘጋጀው እቅድ ቢታቀድም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን እና በአብዛኛው የግንባታ ሳይቶች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ህዳር 30/2009 ዓ.ም ድረስ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዳላገኙ ቢሆንም ኤሌክትሪክ ለማስገባት ቅድመ ክፍያና ለሰብስቴሽን ክፍያ ለኤልክትሪክ ኃይል አገልግሎትድርጅት የተከፈለው ከዚህ በታች በሰንጠረዥ 4 ታይቷል፡፡

| **የግንባታ ሳይት** | **ኪሎ ዋት** | **የተከፈለው** | **የተከፈለበት ቀን** |
|---|---|---|---|
| የኦዳ ቡልቱም | 283.5 | 5000.00 | ሰኔ 15/2008 ዓ.ም |
| የወራቤ | 252 | 5000.00 | ሰኔ 30/2008 ዓ.ም |
| የቦንጋ | 284 | 1,536,217.87 | ግንቦት 4/2008 ዓ.ም |
| የመቅደላ አምባ | 252 | 1,304,261.96 | ግንቦት 6/2008 ዓ.ም |
| የእንጅባራ | 252 | 1,367,252.42 | ግንቦት 4/2008 ዓ.ም |
| የራያ | | 811,191.61 | ግንቦት 4/2008 ዓ.ም |
| የደባርቅ | 252 | 1,260,854.14 | ግንቦት 4/2008 ዓ.ም |
| የደምቢ ዶሎ | | 893,892.58 | ግንቦት 4/2008 ዓ.ም |
| የጂንካ | 252 | 3,341,699.07 | ሰኔ 30/2008 ዓ.ም |

<u>ሰንጠረዥ4</u>. ለካሳ ክፍያ የተያዘው በጀት ከተከፈለው ጋር ማነጻጸሪያ፡፡

- ከላይ በሰንጠረዥ የግንባታ ሳይቶች የተመለከቱት ክፍያዎች የተፈጸመ ሲሆን በተጨማሪም ለሰላሌ እና ለቀብርደሃር ዩንቨርሲቲ ግንባታ ሳይቶች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት እስከ ህዳር 30/2009 ዓ.ም ድረስ ለኤሌክትሪክ ኃይል፣ ትራንስፎርመርና ለዝርጋታ የሚያስፈልገው በጀት ያልተገመተና ክፍያም ያልተፈጸመ መሆኑን፣

- ለአስራ አንዱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ሳይቶች የሚያስፈልገው የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በ2008 በጀት ዓመት አራተኛው ሩብ ዓመት 50% ለማሟላት በነሐሴ 2007 ዓ.ም በተዘጋጀው እቅድ እና በጥቅምት 2008 ዓ.ም ተከልሶ በተዘጋጀው እቅድ ቢታቀድም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ዩኒቨርሲቲዎቹ ተማሪዎችን ተቀብለው ማስተማር ሲጀምሩ የሚያስፈልጋቸውን የመጠጥና የጽዳት ውሃ አቅርቦት ሥራ የጥናት፣ የዲዛይን እና የጉድጓድ ቁፋሮ ዩኒቨርሲቲዎቹ በሚቋቋሙባቸው የክልል የውሃ ሀብት ቢሮዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱን ወክለው እንዲያስፈጽሙ ጥያቄ ቀርቦ ለኦዳቡልቱም ግንባታ ሳይት በሰኔ 14/2008 ዓ.ም ብር 269,243.52 ለኦሮሚያ ውሃ ሃብት ቢሮ፣
- ለጂንካ፣ ቦንጋና ወራቤ ዩኒቨርሲቲዎች በሰኔ 30/2008 ዓ.ም ብር 242,298.00 ለደቡብ/ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል መንግስት ውሃ ሃብት ቢሮ እንዲሁም፣
- ለራያ ዩኒቨርሲቲ በግንቦት 09/2008 ዓ.ም ብር 269,243.52 ለማይጨው ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ክፍያው የተፈጸመላቸው መሆኑ፣
- ለቀሪዎቹ ስድስት ዩኒቨርሲቲዎች ውሃ ለማስገባት ክፍያቸው ያልተፈፀመ መሆኑን እና
- በሁሉም ሳይቶች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ህዳር 30/2009 ዓ.ም ድረስ ውሃ ያልገባላቸው መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የወራቤ፣ እንጂባራ እና ራያ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች፣ አማካሪ ድርጅት ኃላፊዎች፣ የግንባታ ስራ ተቋራጮች፣ የዞን እና ከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች እንዲሁም የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተቆጣጣሪ መሐንዲስ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት ምላሽ እንዲሁም የፕሮጀክት ግንባታ ሂደቶችን የሚያስረዱ መረጃዎችን በመከለስ እና ሁኔታውን በኦዲት የመስክ ስራ ወቅት በአካል ለማየት ተችሏል፡፡

69. ስለሁኔታው የትምህርት ሚኒስቴር መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል አገልግሎት የግምት ስራው ለመስራት በጣም ስለዘገየ በመሆኑና እስከ ህዳር 22/2009 ዓ.ም ድረስ ግንባታ ሳይቶቹ አገልግሎቱ እንዳላገኙና በደቡብ ብ/ብ/ክ/መ ውስጥ እየተገነቡ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች ለግንባታ የሚሆን የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ቢጠየቅም እስከ 30/06/09 አገልግሎቱን ባለማግኘታቸው በግንባታው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳሳደረ እንዲሁም በቀብሪ ደሃር ዩኒቨርሲቲ

የዘላቂ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን በሚመለከት የጥናት ጊዜው ስለተጓተተ ከክልሉ በጊዜያዊነት ቀደም ሲል የጎለበቱ የመጠጥ ውሃ ጉድጓዶችን እንዲጠቀሙ ክትትል እንደሚደረግ ለረቂቅ ሪፖርቱና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገው ውይይት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

70. ለግንባታ ስራው በታቀደው ጊዜ መጠናቀቅ መሰረታዊ ግብዓት የሆኑት የውሃ እና የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት አቅርቦቶች ባለመሟላቱ የአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በእቅዱ መሰረት እንዳይጓዝ ከማድረጉም በተጨማሪ ተቋሞቹ ተጠናቀው የትምህርት ሂደቱን እንዳይጀመር አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

**የስታንዳርድ እና ዝርዝር ዲዛይን (Standard and Detail Design) ስራዎች በተመለከተ፣**

71. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ስታንዳርድ ዲዛይን ከአካባቢው ሁኔታ ጋር በማጣጣም ሊከለስ እና በዕቅዱ መሰረት ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡

72. ይሁን እንጂ ዝርዝር ዲዛይኑን እና የዲዛይን ማጣጣም ስራ በ2008 ዓ.ም በሦስተኛው ሩብ ዓመት (ከጥር እስከ መጋቢት 2008) ለማጠናቀቅ ቢታቀድም፡

**የዲዛይን ጥናት በዕቅዱ መሰረት አለመከናወኑን፡**

- የግንባታ ዝርዝር ዲዛይን ኦዲቱ እስከተከጠናቀቀበት ጊዜ (ህዳር 30/2009 ዓ.ም) ድረስ አለመጠናቀቁ፣
- የስታንዳርድ ዲዛይን ሥራ በ2008 በጀት ዓመት በአንደኛው ሩብ ዓመት 30% በሁለተኛው ሩብ ዓመት 100% ለማጠናቀቅ ቢታቀድም ዘግይቶ ከኤም.ኤች እንጂነሪንግ ፒ.ኤል.ሲ (MH Engineering P.L.C.) ጋር ውለታ የተፈጸመው በታህሳስ 18/2008 ዓ.ም (በታህሳስ 28, 2015 እ.ኤ.አ) እና የተጠናቀቀ በሰኔ 21/2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ ሰኔ 28/2016) ሲሆን የግንባታ ዝርዝር ዲዛይን በ2008 ዓ.ም በሦስተኛው ሩብ ዓመት ለማጠናቀቅ ቢታቀድም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ህዳር 2009 ዓ.ም ድረስ ሥራው እንዳልተጠናቀቀ፣
- ኤም.ኤች እንጂነሪግ ፒ.ኤል.ሲ (MH Engineering P.L.C.) ውለታ ፈጽሞ ዲዛይኑን ሙሉ በሙሉ ጨርሶ በመጋቢት 2008 ዓ.ም (መጋቢት 2016 እ.ኤ.አ) ማስረከብ ሲገባው የውሉ አካል የሆኑትን Preliminary Soil Test Program, Test Pits Excavation, Sampling and Interpretation of Soil

Test Investigation Result, New Typology Building Mainly Laboratory Science & Technology Fields, Lecture Halls, Bed Room and Toilet ሥራዎችን ሶስት ወራት ዘግይቶ በሰኔ 28/2008 ዓ.ም ያጠናቀቀ መሆኑን፣

- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የዲዛይን ማጣጣም (Design Adaptation) ስራ በእቅዱ መሠረት እንዳልተጠናቀቁ ለአብነትም በወራቤ እና በእንጅባራ ዩንቨርስቲዎች የዲዛይን ማጣጣም ሥራው በኮንትራት ውለታው መሰረት በተቀመጠለት ጊዜ ያልተጠናቀቀ እና እስከ ጥቅምት 2009 ዓ.ም ድረስ የጥበቃ ቤቶችም (Guard House) ዲዛይን አለመጠናቀቁን፣
- ዝርዝር ዲዛይንና ቁጥጥር ስራ ከሚሰሩ አማካሪዎች ጋር ውል የተገባው መጋቢት 12/2008 ዓ.ም መሆኑ፣
- ከሥራ ተቋራጮች ጋር ውል የተገባው ለቀብሪ ደሃር ዩኒቨርሲቲ ሰኔ 27/2008 ዓ.ም ሲሆን ለተቀሩት ዩኒቨርሲቲዎች ሚያዚያ 25/2008 ዓ.ም መሆኑን፣
- እንዲሁም የዲዛይን ማጣጣም ስራ እስከ ህዳር 2009 ዓ.ም ድረስ እንዳልተጠናቀቀ፣

**ለዲዛይን የተያዘው በጀት እና ጥናት አተገባበርን በተመለከተ፡**

73. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ስታንዳርድ ዲዛይን ከአካባቢው ሁኔታ ጋር በማጣጣም ሊከለስ እና በውሉ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለዲዛይን ማሰሪያ ተፈላጊው በጀት በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊመደብ ይገባል፡፡

- ማስፈፀሚያ ዕቅዱ ላይ ስታንዳርድ ዲዛይን ለማዘጋጀት የተያዘው በጀት ብር 9,000,000.00 ቢሆንም ከኤም ኤች ኢንጂነሪንግ (ከዋናው አማካሪ) ውል ሲገባ ግን ብር 12,494,751.12 ከበጀት በላይ ብር 3,494,751.12 (38%) የተዋዋሉ መሆኑ ለዲዛይን የተያዘው በጀት በጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን እንደሚያሳይ፣
- ለ11 አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ዲዛይን ማጣጣምና ቁጥጥር የሚሰሩ አማካሪዎች ክፍያ ተብሎ የተያዘው በጀት ብር 28,600,000.00 ሲሆን ከድርጅቶቹ ጋር ውል ሲፈራረሙ ብር 117,668,636.09 በመሆኑ ብር 89,068,636.09 (311%) በብልጫ የተዋዋሉ መሆኑ ለዲዛይን ማጣጣምና ቁጥጥር የተያዘው በጀት በጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን እንደሚያሳይ፣

- የራያ ዩኒቨርስቲ ማስተር ፕላን እንደገና እየተዘጋጀ መሆኑ፣ የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የዲዛይን ለውጦች ለመጥቀስ ያህል የተማሪዎች መማሪያ ክፍል፣ የመጋዘንና ማዕከላዊ ቤተ-መጻሐፍት በተለያዩ ምክንያቶች መለወጣቸው፣
- በዋና አማካሪው (MH Engineering P.L.C.) እና በአስራ አንዱ ዩኒቨርስቲዎች አማካሪ ድርጅቶች መካከል በስታንዳርድ እና ዝርዝር ዲዛይኖች ላይ ልዩነቶች ያሉ ሲሆን ተቋራጮች በልዩነቱ እንደሚያዋጣቸው እየሰሩ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ መግለጻቸው፣
- እስትራክቸራል ዲዛይን እና አርክቴክቸራል ዲዛይን (Structural Design and Architectural Design) ላይ ትልቅ ልዩነት (የዳይሜንሽን ችግሮች እና ስትራክቸራል ዲዛይን ላይ በብረት የሆነው አርክቴክቸራል ዲዛይን ላይ በኮንክሪት የማሳየት ችግሮች) መኖራቸው እንዲሁም Overlap ያደረጉ Pad (ህንጻዎቹ በመሬት ላይ የሚያርፉበት ቦታ) መኖራቸው ግንባታው በልዩነቱ እንዲሰራ ከማድረጉም በላይ እንዲሁም እንዲጓተት እና ተቋራጮች ላላስፈላጊ ወጪ እንዲያወጡ ማድረጉ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

74. ስለጉዳዩ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የምህንድስና ጉዳዮች ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠይቀው ለአማካሪዎችና ተቋራጮች የፋይናንሺያልና ቴክኒካል ውጤት ሲገለፁ የተነሱ ቅሬታዎች ስለነበሩና የነበረው ምልልስ ጊዜ ሊወስድ የቻለ በመሆኑ እንዲሁም ወቅቱ ክረምት ስለነበር ግንባታውን እንደተፈለገ ማስኬድ አለማስቻሉ በግንባታው ፍጥነት ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ ምላሻቸውን ገልጸዋል፡፡

75. ስለሁኔታው የትምህርት ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ስታንዳርድ ዲዛይን ስራ በታቀደው ጊዜ እንደተዘጋጀ እና መጀመሪያ በሁለተኛው ሩብ አመት ለማጠናቀቅ የታቀደ በመሆኑና በዕቅዱ መሰረት ውል ባለመፈራረማቸው በታሰበው ጊዜ ስራውን አላጠናቀቀም መባሉ ትክክል አለመሆኑን፣ በጀቱ የተያዘው ቀደም ብሎ ስለሆነና ጨረታው የተካሄደው ደግሞ ከዚያ በኋላ በመሆኑ ምክንያት የተከሰተ ክፍተት መሆኑን ለረቂቅ ሪፖርቱ እና በመዉጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ግኝቱን እንደግብዓትነት እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ለሌሎቹ ጉዳዮች ምላሽ አልሰጡም፡፡

76. ኃላፊዎቹ ይህን ከላይ የተጠቀሰውን የማስተባበያ አስተያየት ቢሰጡም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ከየፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ከተሰበሰበው መረጃ ግኝቶቹ ትክክል መሆናቸውን የሚያሳዩ በመሆናቸው የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

77. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ስታንዳርድ ዲዛይን ከአካባቢው ሁኔታ ጋር የማይጣጣሙ እና በዕቅዱ መሰረት ሊጠናቀቁ ባለመቻላቸው በዕቅዱ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ ግንባታዎች ተጠናቀው 2010 ዓ.ም እያንዳንዳቸው 1500 በድምሩ 16500 ተማሪዎችን ተቀብለው የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማስጀመር አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## 2.3 የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ግብዓቶች እና ሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት በዕቅድ መርሃ ግብር መሰረት መሆኑን በተመለከተ፤

**የአስራ አንድ አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ተጠናቆ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማስጀመር መሟላት የሚገባቸው ግብዓቶችን በተመለከተ፣**

78. ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች መምህራን ልማት የወጣው ዕቅድ በሚፈለገው መጠንና በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሊከናወን ይገባል፡፡ በዕቅድ መሠረት የተማሪ ቅበላ አከናውኖ ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚያገለግሉ ግብዓቶች/ መጽሐፍቶች፣ የላብራቶሪ ቁሳቁሶች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ የተማሪ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ወ.ዘ.ተ…/ የአቅርቦት ዕቅድ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

79. ይሁን እንጂ ለአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች መምህራን ልማት በሚፈለገው መጠን እየተከናወነ አለመሆኑ እንዲሁም በዕቅድ መሠረት የተማሪ ቅበላ አከናውኖ ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚያገለግሉ ግብዓቶች እየተሟሉ አለመሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ

- ዩኒቨርሲቲዎቹ የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታ ሲጠናቀቅ የሚያስፈልግ መምህራን ብዛት በተጠናው መሰረት ለ2010 ዓ.ም ከ2007 ዓ.ም ተመራቂዎች 825 ዕጩ መምህራንን ለማሰልጠን ቢታቀድም 623 የዕቅዱ (75.5%) መምህራን ብቻ እየሰለጠኑ መሆኑ፣
- የግንባታ ግብዓት ግዥ በ2008 በጀት ዓመት በሁለተኛው ሩብ ዓመት ለማከናወንና የግንባታ ግብዓት ስርጭት 30% በሁለተኛው፣ 65% በሶስተኛው እና 100% በአራተኛው ሩብ ዓመት ለማከናወን በ2008 ዓ.ም ተከልሶ

በተዘጋጀው ዕቅድ ቢታቀድም በተባለው ጊዜ አለመፈጸሙን ማለትም የተለያዩ ሚ.ሜ ብረቶች እስከ የካቲት 2008 ዓ.ም ድረስ ከድርጅቶቹ ጋር ውል ታስሮ ያልተገዙና ያልተሰራጨ መሆናቸው፣ ባለ 6 እና 8 ብረቶች እስከ ሰኔ 2008 ዓ.ም ድረስ ግዥው ያልተከናወነ መሆኑ እንዲሁም ሲሚንቶ እስከ መጋቢት 2008 ዓ.ም ድረስ ግዢው ያልተከናወነ መሆኑንና ስርጭቱ ያልተከናወነ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

80. ስለ ጉዳዩ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ የምህንድስና ጉዳዮች ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠይቀው የክረምት ወቅት በመሆኑ እና እንዳንድ ቦታዎች ባለይዞታዎች በወቅቱ ያልተነሱ የነበሩ በመሆኑ የግንባታ ስራው በሚጠበቀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሊሰራ አለመቻሉንና የኦዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታው ስላልተጀመረ እንደማይጠናቀቅ የሌሎችን ግን የዘገዩትን በክራሽ ፕሮግራም እንዲሰሩ በማድረግ ለማጠናቀቅና በቀጣይ አራት አምስት ወራት ከተቋራጭ ጋር የአቅም ችግር ካልተፈጠረ፣ ከግብዓት ጋር በተያያዘ የአቅርቦት ችግር ካልተፈጠረ ግንባታዎቹን ለማጠናቀቅ በቂ ጊዜ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

81. ስለጉዳዩ የትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊዎች የትምህርት መሳሪያዎች ግዥ ረጅም ጊዜ እንደወሰደና አብዛኞቹ የእስፔስፊኬሽንና የስታንዳርድ ዝግጅቱ ተጠናቆ በአሁን ወቅት የግዥ ኤጀንሲ ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር ከ90 እስከ 120 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ግዥውን ለማከናወን በሂደት ላይ እንዳለ ለረቂቅ ኦዲት ሪፖርቱ እና በመውጫ ስብሰባ ውይይት ላይ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

82. ኃላፊዎቹ ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ምላሽ ይግለጹ እንጂ የ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በባለቤትነት የሚመራውና ዕቅዱን የሚያስፈጽመው ትምህርት ሚኒስቴር እና በሚኒስቴሩ ስር የተዋቀረው ፕሮጀክት ጽ/ት ስለሆነ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

83. ለአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች መምህራን ልማት በሚፈለገው መጠን አለመከናወኑ እንዲሁም ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚያገለግሉ ግብዓቶች አለመሟላታቸው በ2010 ዓ.ም እያንዳንዳቸው 1500 በድምሩ 16500 ተማሪዎችን ተቀብሎ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማስጀመር እና የተቀመጠውን የቅበላ እቅድ ለማሳካት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

84. የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም፣ የግንባታ እና ሌሎች ግብዓቶች ለማሟላት የታቀደው ዕቅድ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ መሆኑን ሲገመግም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ የፈፃሚ አካላትን ድርሻ በግልጽ አለመለየቱ፣ እና በባለድርሻ አካላት አለመገምገሙ፣
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎችን የግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) ቢዘጋጅም የግንባታ ግብዓት ሆነ የላብራቶሪና የመጽሐፍት ግዥ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት በዕቅዱ መሰረት ለማከናወን የትግበራ መርሃ ግብር ያልወጣለት መሆኑ፣
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ዕቅድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክቱ እቅድ አፈፃፀም ላይ ያላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ የቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑ፤
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲ ፕሮጀክት ግንባታዎች ስራ ከመጀመሩ አስቀድሞ በግንባታ ሆነ በትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶች ያልተለዩ መሆኑ፤
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጀክት ግንባታን የሚያስፈጽም ጽ/ቤቶች (በትምህርት ሚኒስቴርና በፕሮጀክቶች ሳይቶቹ) የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች ያልተሟላላቸው እና የሥራ ኃላፊነት እና ተግባራት ዝርዝር በጽሁፍ ያልተገለጸላቸው መሆኑን፤
- ዩኒቨርሲቲዎቹ ተገምብተው ሲጠናቀቁ ለአካባቢው ህብረተሰብ እና ለሀገር ያለውን ፋይዳ እንዲሁም የግንባታ ፕሮጀክቶቹ አስፈላጊነት በተመለከተ የግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይት ያልተጠናከረ መሆኑ፣
- የዩኒቨርሲቲዎቹ ግንባታ ፕሮጀክት በአካባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ላይ ሊያስከትሉት የሚችሉትን የተጽዕኖ የግምገማ ጥናት አለመከናወኑ እና ለመልሶ ማቋቋሚያ መርሃ ግብር ጥናት ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤

- ለአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ምክንያት ከግንባታ ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ክፍያ ያልተከናወነ እና ካሳ የተከፈላቸውም የአካባቢው ነዋሪዎች በተቀመጠው ቀነ ገደብ ከቦታው ያልተነሱ መሆኑ፤
- የዉሃ እና የኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት አቅርቦቶች ግንባታዎቹ ከመጀመራቸው በፊት ለአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ሳይቶች ያልተሟሉ መሆኑ፤
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ስታንዳርድ ዲዛይን ከአካባቢው ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልክ በዕቅዱ መሰረት ያልተከለሰ/ የዲዛይን ማጣጣም ሥራው ያልተሰራ መሆኑ፣
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የመምህራን ልማት በሚፈለገው መጠን እየተከናወነ አለመሆኑ እና
- በዕቅዱ መሠረት የተማሪ ቅበላ አከናውኖ ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚያገለግሉ ግብዓቶች (የመማሪያ መጽሐፍቶች፣ የተማሪ ወንበርና ጠረጴዛ፣ የላብራቶሪ ቁሳቁሶች እና ሌሎች) በዕቅዱ መሰረት ግዥው ያልተከናወነ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

85. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

86. የትምህርት ሚኒቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመፍጠር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ሊገነቡ የታቀዱት የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ዕቅድ አፈፃፀም፣ የግንባታ እና ሌሎች ግብዓቶች ለማሟላት የታቀደው ዕቅድ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል እንዲሁም መንግስት ለወደፊት ሊገነባቸው እና ሊያሰፋፋ ለሚያቅዳቸው የተቋም ግንባታ ላይ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ♦ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ አሁንም የግንባታ ምዕራፉ ገና በጅምር ላይ ስለሚገኝ በቀሪ ሥራዎች ላይ ዕቅዱ የፈፃሚ አካላትን ድርሻ የሚለይ እና የሚያሳትፍ እንዲሁም ግንባታው ዕቅዱም በሁሉንም አካላት እንዲገመገምና አስተያየት እንዲሰጥበት ሊደረግ ይገባል፡፡
- ♦ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎችን የግንባታ ፕሮጀክት አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ቀሪ ሂደቱ ዋነኛው መሪ ዕቅዱን (Master Plan) መሰረት በማድረግ እና የድርጊት መርሃ ግብር በማውጣት ተግባራዊ ሊደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የዘገዩ ስራዎች የሚካካሱበትን መንገድ በመቀየስ በዕቅዱ መሰረት የተማሪዎች ቅበላ የሚከናወንበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ♦ የአስራ አንዱ ዩኒቨርሲቲዎች ቀሪ ስራዎችን በማጠናቀቅ በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ለማድረግ የግንባታ ፕሮጀክት ዕቅድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክቱ እቅድ አፈፃፀም ላይ ያላቸውን ሀገራዊ ሃላፊነት እንዲወጡ ለማስቻል ቀጣይነት ያለው እና ችግር ፈቺ የሆነ ጠንካራ የቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ♦ የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት እቅድ ትግበራው ሂደቱ ገና በጅምር ላይ ስለሆነ ለአንደኛውም ሆነ ለቀሩት የግንባታ ምዕራፎች በትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደቱ በዘላቂነት እንዳይቀጥል ሊከሰቱ የሚችሉ ሥጋቶች ተለይተው እንዲቀመጡ እና እንዳይከሰቱ የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎችም ሊሰሩ ይገባል፡፡

- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት የሚያስፈጽም ጽ/ቤቶች በትምህርት ሚኒስቴርና በየፕሮጀክት ሳይቶቹ እንዲቋቋሙ ማድረጉ መልካም ጅምር ቢሆንም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ትኩረት ተሰጥቶት የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶች እንዲሟሉ እንዲሁም የሥራ ኃላፊነት እና ተግባራት ዝርዝር በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ሊደረግ ይገባል፡፡
- አስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎቹ ተገምብተው ሲጠናቀቁ ለአካባቢው ህብረተሰብ እንዲሁም ለሀገር ያላቸው ፋይዳን አስመልክቶ በአካል ከህዝቡ ጋር እንዲሁም ተደራሽና ተደማጭ ሚዲያዎችን በመጠቀም የግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይቶች በማድረግ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖር ሊደረግ ይገባል፡፡
- የዩኒቨርሲቲዎቹ ግንባታ ፕሮጀክት በአካባቢያዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ላይ ያለው ፋይዳ እና ተጽዕኖ በመገምገም ፋይዳው የማጎልበት ሁኔታ የማመቻቸት እንዲሁም ተጽዕኖው የሚቀረፍበት ሁኔታ የማመቻቸት ስራ ሊሰራና በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ከአካባቢው የተነሱት የህብረተሰቡ ክፍሎች ለመልሶ ማቋቋሚያ መርሃ ግብር ጥናት ሊደረግና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
- ለአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ምክንያት ከግንባታ ቦታው ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ክፍያ ያልተከናወነላቸው ነዋሪዎች በህጉና መመሪያው መሰረት እንዲከፈል፣ በካሳ ምክንያት ያላግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ተጣርቶ በአስቸኳይ የሚመለስበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ለካሳ ክፍያ ተብሎ በጥቅል የተላኩ ሂሳቦች እና እስከ ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም ያልተወራረዱ ሂሳቦች በአስቸኳይ ሊወራረዱ ይገባል፡፡ ወደፊትም የሚከፈሉ የካሳ ክፍያዎች በካሳ አዋጁ፣ ደንብ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት ሊፈጸም እና ከህግ ውጭ እንዲከፈል የተደረገው ሂሳብ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
- የአስራ አንድ ዩኑቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ከመጀመሩ በፊት መሟላት የሚገባቸው ወሳኝ የሆኑ የዉሃ እና የኤሌክትሪክ ሀይል አገልግሎት አቅርቦቶች የግንባታ ሂደቱን የሚያጓትቱ በመሆኑ የሚመለከታቸው ትምህርት ሚኒስቴር በአስቸኳይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ወቅታዊ መፍትሄ ሊሰጠው

ይገባል፡፡ በተጨማሪም የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዳይስተጓጎል በቂ የሆነ የኤሌክትሪክ እና የውሃ አቅርቦት በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የሚሟላበት ሁኔታ ለመፍጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በፍጥነት ሊሰራ(ቅንጅታዊ አሰራር ሊያከናውን) ይገባል፡፡

- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ስታንዳርድ ዲዛይን ከአካባቢው ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልክ ተከልሶ ሊዘጋጅ እና በዕቅዱ መሰረት የዲዛይን ማጣጣም ስራ በአማካሪዎች ሊሰራ ይገባል፡፡
- የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የመጀመሪያውን ምዕራፍ ግንባታ ተጠናቆ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማስጀመር እንዲረዳ በትምህርት ሚኒስቴር ትኩረት ተሰጥቶት የመምህራን ልማት እና ሌሎችም የግብዓቶች(የመማሪያ መጽሐፍቶች፣ የተማሪ ወንበርና ጠረጴዛ፣ የላብራቶሪ ቁሳቁሶች እና ሌሎች) ግዥ በፍጥነት ሊከናወን ይገባል፡፡

87. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የትምህርት ሚኒስቴር፣ የወራቤ፣ እንጅባራ እና ራያ ዩኒቨርስቲዎች ስራ አስኪያጆች፣ አማካሪ ድርጅት ኃላፊዎች፣ የግንባታ ስራ ተቋራጮች፣ የዞን እና ከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች እንዲሁም የአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዋና ስራ አሲኪያጅ እና የምህንድስና ጉዳዮች ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1) የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ዕቅድ ዝግጅት ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የተስማሙበት ግልጽና ሥራዎች የሚከናወኑበት የጊዜ ገደብ የተቀመጠላቸው አሳታፊና ሊተገበር የሚችል መሆኑን መገምገም፣ | 1. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ የፈፃሚ አካላትን ድርሻ የሚለይ እና የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 2. የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት (ግንባታዎቹ በምዕራፍ ተከፋፍለው መቼ እንደሚሰሩ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ፣ ፕሮጀክት ፅ/ቤቶች የት እንደሚቋቋሙ፣ ለካሳ ክፍያ የተያዘው ወጪ፣ ለቅድመ ግንባታ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችና ወጪዎች፣ የባለድርሻ አካላትን ሚናቸውን መለየቱን…) የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 3. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ ትግበራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ በወር፣በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት እንዲሁም በዓመት ተከፋፍሎ ሊተገበር በሚችል መልክ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ |
| | 4. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ ዕቅድ በሁሉም አካላት ሊገመገምና አስተያየት ሊሰጥበት ይገባል፡፡ |
| | 5. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ግንባታ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 6. ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክቱ እቅድ አፈፃፀም ላይ ያላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ በቅንጅት መስራት አለባቸው፡፡ |
| 2) የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በዕቅዱ መሠረት በመተግበር የተማሪ ቅበላ ሂደቱ በተቀመጠለት የዕቅድ መርሃ ግብር መሰረት የሚከናወን መሆኑን መገምገም፤ | 7. ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የግንባታው ሂደት ከመጀመሩ በፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን (Risks) በቅድሚያ በማጥናትና በመለየት ሥጋቶቹ እንዳይከሰቱ ቅድመ ጥንቃቄ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 8. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ስታንዳርድ ዲዛይን ከአከባቢው ሁኔታ ጋር በማጣጣም ሊከለስ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 9. የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ኘሮጀክት ግንባታን የሚያስፈጽም ጽ/ቤቶች በትምህርት ሚኒስቴርና በፕሮጀክቶች ሳይቶቹ ሊቋቋሙ እና በተገቢው ግብዓቶች ሊደራጁ ይገባል፡፡ |
| | 10.አሥራ አንዱም የግንባታ ኘሮጀክት ጽ/ቤቶች የሥራ ኃላፊነት እና ተግባራት በዝርዝር ሊገለጽ ይገባል፡፡ |
| | 11.ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉ መስተዳደር እና ሌሎች የግንባታ ፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለአካባቢው ሕብረተሰብ ስለዩኒቨርሲቲዎቹ ጥቅም የግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይት ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 12.የአካባቢና የማህበራዊ ሁኔታ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት እና ለመልሶ ማቋቋሚያ መርሀ ግብር ጥናት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 13.ለ11 ዩኒቨርሲቲዎች የኘሮጀክት ግንባታ ምክንያት ለሚነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች በተፈቀደው የካሣ ሕግና መመሪያ መሰረት ካሣ ሊከፈል ይገባል፡፡ |
| | 14.ካሳ የተከፈላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች የካሣ ክፍያ ከተፈፀመላቸው በኋላ ከቦታቸው በተቀመጠው ቀነ ገደብ መነሳት አለባቸው፡፡ |
| | 15.ለ11 ዩኒቨርሲቲዎች የሚያገለግል የዉሃ፣ የኤሌክትሪክ ሀይልና የቴሌኮም አገልግሎት ግንባታው ከመጀመሩ በፊት ሊሟሉ ይገባል፡፡ |
| | 16.የአማካሪዎችና የተቋራጮች መረጣ በመንግስት ህግና ደንብ መሰረት ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 17.ለሚሰሩት ሥራዎች ውል ሊገባና በውሉ መሠረት ስለመሰራታቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 18. ለግንባታው የሚያገለግሉ ዕቃዎችና አገልግሎት ግዥዎች በተቀመጠው ዕቅድ መሰረት በመንግስት የግዥ ህግና መመሪያ መሠረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ |
| | 19. በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የግንባታ እቃዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | 20.ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የፕሮጀክት ግንባታውን የሚቆጣጠርበት፣ የሚከታተልበት እና የሚገመገምበት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ አዘጋጅቶ ሥራ |

| | |
|---|---|
| | ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ |
| | 21.በአማካሪ መሐንዲሶችና በስራ ተቋራጮች ወሪሃዊ የስራ ክንውን ሪፖርት ለዋና ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሊቀርብ ይገባል፡፡ |
| | 22.በየሳይቱ ያሉ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች የግንባታውን አተገባበርና አፈፃጸም ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱና በትምህርት ሚኒስቴር ለተቋቋመው የኘሮጀክት ግንባታ ጽ/ቤት በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ እና በየስድስት ወሩ ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ |
| 3) የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ግብዓቶች እና ሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት የዕቅድ መርሃ ግብር መሰረት የሚከናወን መሆኑን መገምገም፤ | 23.ለ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ የሚውሉ ግብዓቶች /ድንጋይ፣ አሸዋ፣ ብሎኬት የመሳሰሉት…./ ምንጫቸው ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል፡፡ |
| | 24.ለ11 ዩኒቨርሲቲዎች መምህራን ልማት የወጣው ዕቅድ በሚፈለገው መጠንና በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 25.በዕቅድ መሠረት የተማሪ ቅበላ አከናውኖ ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚያገለግሉ ግብዓቶች/መጽሐፍቶች፣ የላብራቶሪ ቁሳቁሶች፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ የተማሪ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ወ.ዘ.ተ…/ የአቅርቦት ዕቅድ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

# የትምህርት ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር አባሪ 2

